

ግዕዝ ፊደል



የኢ/ል/ቴ/ዩ/ግቢ ጉባኤ ከኔ ጋር ይማሩ



ድርሰት ፦ ኃይሉ መልካሙ

ፅሑፍ፦ ፋሲል ኪዳኔ

የደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ እና ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን ሥዓተ-ጥበብ ሰ/ት/ቤት

ተዋንያን

ደ/በረከት ቅዱስ ገብርኤል ቤ/ክ ፈለገ ቅዱሳን ሰ/ት/ቤት

ዮሐንስ ፦ አዲስዓለም ጌቱ

አቶ ጌታቸው ፦ እንጆሪ ገዛኸኝ

ብርቄ ፦ ሳራ ገብሬ

እመቤት ፦ መቅደስ ብስራት

ዳዊት ፦ ሔኖክ ምትኩ

ሶስና ፦ ቤዛ ለማ

አዘጋጅ ፦ አማረ ተመስገን

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

የቅ/ሔ/ዩ/ግቢ ጉባኤ ገጽ ማኅበረ ክፍል

(ብዙም እውቀት የሌላቸው ሳይማሩ ቤተሰባቸውን ያስተማሩ አባት አቶ ጌታቸው በጠዋት ቤት ውስት ተቀምጠው ሲተክዙ ይታያሉ)

እመቤት፦ (ከመኝታ ቤት ወጥታ ጀስ አምዋታ ትሰጣቸዋለች) ት.....ዕ.....ይ.....ን.....ት (ጀ) /አ...ን..ድ.../

አቶ ጌታቸው፦ (ጀርባቸውን ይሰጧታል)

ዳዊት፦ (ይገባል)

እመቤት፦ (ጁሱን አስቀምጣ ትወጣለች)

አቶ ጌታቸው፦ (ጁሱን እያየ ይተክዛሉ)

ዮሐንስ፦ (ከውጪ በቁምጣ ይገባል) ደህና አደርክ ፋዘር?

አቶ ጌታቸው፦ (በአትኩሮት ይመለከቱታት)

ዮሐንስ፦ እንዴ ጀስ .... (ደንግጠዋል) .... አባት ማለት አንተ ነህ... ስፖርተኛ ፈላሽ እንደሚያስፈልገው ታውቃለህ የእውነት ኮራውብህ

አቶ ጌታቸው፦ ዝምበል ማፈሪያ ለመሆኑ ዝየት ነው የምትመጣው?

ዮሐንስ፦ ማንን እኔን ነው ፋዘር?

አቶ ጌታቸው፦ አይ ጥላህን ነው

ዮሐንስ፦ እንዴ ፋዘር አረጀህ እንዴ አስባስሴ ከስፖርት እንደመጣው አይገልፅም ይሔን አውቀህ አይደል እንዴ ጀስ አዘጋጅተህ የጠበከኝ።

አቶ ጌታቸው፦ አ.....ሀ... ለልጅ ይገለፅለት አይደል።

ዮሐንስ፦ አሁን ነገሩን አመጣኸው /ወደ አሳቸው እየተጠጋ/ እንደው ለልጆችህ እያሰብክ ወጉርህ ሸበተ እንጂ ገና ልጅ ነህ

አቶ ጌታቸው፦ /አኖገፈተሩት/ ስፖርቱን የምትሰራው ለጤንነት ነው ወይስ ጤናን ለማቃወስ?

ዮሐንስ፦ ስፖርት ለጤንነት ነው እንጂ ጤናን ለማቃወስ ይሰራል እንዴ?

አቶ ጌታቸው፦ እኔ ምን አውቃለው መልሶ ይጠይቀኛል እንዴ?

ዮሐንስ፦ ማብራሪያ አለኝ ፋዘር ጥያቄህ ገብቶኛል ላቤ ስለሸተተህ ነው አይደል ይኼው ፋዘር ላብ የድካምና ብዙ የመስራት ውጤት ነው።

አቶ ጌታቸው፦ ታዲያ ያንተ ላብ ለየት ያለ ነው?

ዮሐንስ፦ እንዴት ፋዘር?

አቶ ጌታቸው፦ ዝናም ዘንቦ ነው እንዳልል ዝናም የለም ላብ ነው እንዳልል የሰው ጠረን አይደለም እና ምንድነው ይሔ?

ዮሐንስ፦ እንዴ አባዬ ጠጥተሃል ለማለት ነው?

አቶ ጌታቸው፦ አረ በፍፁም

ዮሐንስ፦ እና ታዲያ?

አቶ ጌታቸው ፦ ማራቶን እየሮጥክ አልነበር?

ዮሐንስ፦ አዎን

አቶ ጌታቸው፦ እነዚያ በቴሌቪዥን ሲሮጡ የምናያቸው ሲደክማቸው ውሃ ጠጥተው እራሳቸው ላይ ይደፉ የለ?

ዮሐንስ፦ አዎን

አቶ ጌታቸው፦ አንተም እንግዲ ሌሊት ስትሮጥ ደከመህና አላይ ላይ ደፋህው

ዮሐንስ፦ ያራዳ ልጅ ነህ እኮ ፋዘር

አቶ ጌታቸው፦ ግን ያንተ ተለየ

ዮሐንስ፦ ተለየ?

አቶ ጌታቸው፦ አዎ

ዮሐንስ፦ እንዴት?

አቶ ጌታቸው፦ ምን እንዴት ትላለህ ላንተ የተቀመጠልህ ኮዳ እንስራ ነበር እንዴ?

ዮሐንስ፦ እንስራ?

አቶ ጌታቸው፦ አዎ እንስራ ጠጅ ጠጅ የሚል ላብ በሕይወቴ ዛሬ ነው ያየውት

ዮሐንስ፦ ጠጅ ጠጅ ምን ነካህ አባዬ በዚህ ሰዓት ጠጅ ለምን በጊዜ ገባህ ነው አይደል አብረን መግባታችንን እያወክ ደህና አደር ዮሐንስ ብለኸኝ ደህና አደር አባዬ ብዬህ አይደል የተኛውት?

አቶ ጌታቸው፦ በል አታላዝንብኝ ሳይንጋብህ ግባና ተኛ

ዮሐንስ፦ አባዬ አላመንክኝም አይደል .... ካላመንክ ብርቄን ጠይቃት እሷ ነች ሌሊት የቀሰቀሰችኝ

አቶ ጌታቸው፦ የራስህ ሳያንስህ ለምን ሰውን ኃጢአት ውስጥ ትከታለህ ከሌሊቱ 11 ሰዓት ጀምሮ እዚህ ቁጭ ብያለው በየት ወጣህ?

ዮሐንስ፦ ይችህ ብርቄ ነች አባዬ ተኝቷል እኔ እንግረኃለው ብላ 10 ሰዓት ላይ የቀሰቀሰችኝ ለቁልፍ ብዬ ከምቀሰቅሰህ ለዛሬ በአጥር ወጣው እሷ ብርቄ ሸኝታኝ ነው የሄድኩት ካላመንክ ጠይቃት ማርያምን

አቶ ጌታቸው፦ ዝም በል አንተ በአንተ አፍ ማርያምን አትበለኝ አዛኝ ነች አትቀጣኝም ብለህ ነው አይደል እኔ ግን አፈራልሃለው ይህ ሁሉ መሃላህና ግዝትህ አንድ ቀን ዋጋ ያስከፍልሃል።

ብርቄ፦ ደህና አደርክ አባዬ? /ወተት እየሰጠቻቸው/

አቶ ጌታቸው፡- ደህና አደርሽ ብርቁ
ብርቁ፡- አ....አ... እንዴ በቁምጣ አ... ሀ... በቆዳ ጫማ
አቶ ጌታቸው፡- ብርቁ
ብርቁ፡- አቤት አባዬ
አቶ ጌታቸው፡- ከስፖርት ነው የመጣው ወተት አምጭለት
ብርቁ፡- ከስፖርት?
ዮሐንስ፡- /እጁን አንስቶ ሲለምኑት አባቱ ሲያዩት እጁን ወደ ላይ እየዘረጋ ስፖርት ሲሰራ ይታያል/
አቶ ጌታቸው፡- ምንድነው እንደዚህ የሚያስታት?
ዮሐንስ፡- ውፍረቴን አይታ ገርሟት ነው
አቶ ጌታቸው፡- በል ግባና ልብስ ልበስ በኋላ ብርድ ቢመታህ ለመርፌ የሚሆን ሥጋ የለህም
ዮሐንስ፡- /ሰውነቱን እያየ/ በዚህ በዚህ እንኳን አንታማም
አቶ ጌታቸው፡- ኧረ አንተን በምን በምን አምቼ እዘልቅሃለው
ዮሐንስ፡- ምን አልክ አባዬ?
አቶ ጌታቸው፡- ወተት መጥቷል
ዮሐንስ፡- አይ ብርቅዬ ነፍስ አኮ ነሽ አንቺ ብርቅዬ .....
ብርቁ፡- /አፍንጫዋን ይዛ ወደ ኋላ ትሸሻለች/
ዮሐንስ፡- ብርቅዬ እንስሳ
ብርቁ፡- /በዝግታ/ አንቡላ
ዮሐንስ፡- ይችህ ልጅ እንዴት አባቷ ነው የጠገበችው?
አቶ ጌታቸው፡- ደግሞ እሷ ምን አደረገችህ?
ዮሐንስ፡- ቆይ እኔን በታይ ለምንድነው የምትሸሸው? ምን ሆና ነው?
አቶ ጌታቸው፡- አፍህ ማስቲካ ማስቲካ ሽታት ነዋ
ዮሐንስ፡- ምን አልክ ፋዘር?
አቶ ጌታቸው፡- ምነው ቅድም ሽኝችኝ ምናምን ስትል አልነበረም?
ብርቁ፡- የምን ሽኝት?
ዮሐንስ፡- አዲሱ የስፖርት ስም ነው /እየዘለለ/
ብርቁ፡- ታዲያ በግንባርህ ነው እንዴ የምትሰራው?
ዮሐንስ፡- ከሰው ለየት ለማለት ነዋ
ብርቁ፡- ታዲያ የእኔን ሽኝት ምን አመጣው?
አቶ ጌታቸው፡- ማታ እኔን ላለመቀስቀስ የሸኝሽው ነዋ?
ብርቁ፡- ማን? .....እኔ?
ዮሐንስ፡- አይ እኔ ..... ሂጂ በር ከፊቼ በር እየተንኳኳ አይደል
አቶ ጌታቸው፡- ኧረ ተው አንተ ልጅ ልጅቷን አታብጠልጥላት
ዮሐንስ፡- አይ ፋዘር እሷ ነች እንጂ የምታብጠለጥለኝ .... ለዚህ ሁሉ ደግሞ ተጠያቂው አንተ ነህ
አቶ ጌታቸው፡- ደግሞ እኔ ምን አደረኩ?
ዮሐንስ፡- የቤቱ ሁሉ ሃላፊነት በእንቺ ነው እያልክ ፈልጭ ቆራጭ አደረካት ታዲያ እንዴት አታብጠልጥለኝ እኔኮ ያልገባኝ ነገር ለምን እንደሰራቶኛ አትኖርም።
አቶ ጌታቸው፡- የአንተ ጥላቻ ይገባኛል ቤቱን ለመዘጋዘት እንዲያመችህ ነው እኔ ግን ከልጅቼ ለይቼ አላያትም።
ዮሐንስ፡- ነው እንዴ እህ.... ምን ትንሻከኪያለሽ አቤት አንቺና ወሬ ውይ...ውይ መቼ ይሆን የወሬ ነዳጅሽ የሚያልቀው
ብርቁ፡- አንተ እውነት ግን ከስፖርት ነው የምትመጣው?
ዮሐንስ፡- ሌላ ወሬ .... ወይኔ በእናትሽ መቼ ነው ባትሪ ሎው የምትይው
ብርቁ፡- ውሸትህን ስዊች ኦፍ ስታደርገው
ዮሐንስ፡- እንዴ /በአግራሞት ይመለከታታል አፋን ይይዛል/
ብርቁ፡- አዎ አሁን ንገረኝ ከስፖርት ነው የመጣኸው?
ዮሐንስ፡- /አንገቱን በአወንታ ይነቀንቃል/
ብርቁ፡- ምን አይነት ስፖርት ስትሰራ ነበር?
ዮሐንስ፡- ሰርከስ
አቶ ጌታቸው፡- አሁን አምስት ሺህ አስር ሺህ ስትል አልነበር?
ብርቁ፡- አውቆ ነው
ዮሐንስ፡- እውነቱን ነው
ብርቁ፡- አባት ይዋሻል?
ዮሐንስ፡- ይዋሻል
አቶ ጌታቸው፡- ምን አልክ?
ዮሐንስ፡- አይዋሽም
ብርቁ፡- አንተ ግን ውሸታም ነህ
ዮሐንስ፡- አጋብተሽብኝ ነው
ብርቁ፡- ማን? እኔ?
ዮሐንስ፡- አይ እኔ ሞጭሟጣ
ብርቁ፡- አንቡላ /በለሆሳስ/
ዮሐንስ፡- አየሃት አባዬ ስትሰድበኝ
አቶ ጌታቸው፡- መቼ?
ዮሐንስ፡- አሁን
አቶ ጌታቸው፡- ምን ብላ?
ዮሐንስ፡- አንቡላ
አቶ ጌታቸው፡- በርሜልም አለማለቷ እሷ ሆና ነው
ዮሐንስ፡- ምን አልክኝ አባዬ?
አቶ ጌታቸው፡- ነገሩ ወዲህ ነው የጠየቀችህን አንዲት ጥቂያ ለምን አትመልስላትም
ዮሐንስ፡- ማነች እሷ?
አቶ ጌታቸው፡- ብርቁ
ዮሐንስ፡- ምን ብርቁ ነች ይችህ ድርቁ ዓት አንጂ።
ብርቁ፡- መልሰልኝ?
ዮሐንስ፡- ምኑን?
ብርቁ፡- ጥያቄዬን?
ዮሐንስ፡- ይለፈኝ
ብርቁ፡- መልስልኝ?
ዮሐንስ፡- ይ..ለ...ፈ..ኝ ..... ተመለሰልሽ?
ብርቁ፡- አምን በትክክል መልሶታል ይሄ የማን ቦርሳ ነው?
ዮሐንስ፡- ብርቁ ....ብርቁ
ብርቁ፡- አባዬ መጀመሪያም ጠርጥሪያለው በቆዳ ጫማ ስፖርት የት ሃገር ነው የሚሰራው እስከመቼ ነው ከራስህ ጋር የምትጣላው እስከመቼ በውሸት ትኖራለህ እስኪ አስበው አንተን ተስፋ የሚያደርገው አባትህ የአንተን ከፉ ሞት ቢሰማ ምን ይውጠዋል።
አቶ ጌታቸው፡- ብርቁ በጠዋት ጥሩ ጥሩ ነገር አውሪ እንጂ
ብርቁ፡- ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ አንተ ነህ አባዬ ሁሉጊዜ እያወክ የሱን ውሸት ትቀበልዋለህ ዛሬ በቁምጣ ልብሱን ተዘርፎ መጣ ነገ ራቁቱን ይመጣል ከነገ ወዲያስ.... ጥሩ ሰው አጋጥሞት ነው እንጂ መጥፎዎች ቢሆኑ ወይ በድንጋይ ወይ በጩቤ ሰንት ነገር አለ መሰለህ አባዬ ተመልከት የሰፈር ሰዎች ናቸው ይሄን የሰጡኝ ዛሬ ልብሱ መጣ ነገ እርቃኑን ቢወድቅ ማነው ተጠያቂ እኔ አባዬ ወይስ አንተ .... አውቃለው ይሄን ለመናገር ስልጣኑ እንደሌለኝ እንደ እኔ ስላሰብኩ ነው ዮሐንስ ይቅርታህን ተስፋ አደርጋለው /ትወጣለች/
አቶ ጌታቸው፡- ትልቅ ሰው ነች እኛን እንደሷ ቆጥራ ተናገረች አንተ የሰጠሃት ቦታ ግን ምንድነው ሰራተኛ በእርግጥ ጥፋቱ የእኔ ነው ከዛሬ ነገ ትለወጣለህ እያልኩ ያንተን ውሸት ታገስኩኝ አሁን ግን ነገሩ አፍጥጦ መጣ የእኔም ፍቅር ላንተ የመበላሸት ምክንያት ሆነ እንደው እግዚአብሔር አያድርገውና አንተ አንድ ነገር ብትሆን በሰማይ ቤት ወቀሳው በእኔ እንደሚበረታ አታውቅም ኧረተው ተለመነኝ ልጂ እኔም እኮ በአንተ የተነሳ ውሸታም ሆንኩ አሁን ወንድምህ ቢሰማ ምን ይላል።
ዳዊት፡- ሁሉንም ነገር ሰምቸኋለው አባዬ አሁን አንተ ዝም ትላለህ እንደሌላው ጊዜ በእኔና በእርሱ መሃል እንዳትገባ አየኸው አይደል የማቅበጥህ ውጤት ስንት ጊዜ በእንተና በማርያም ስም ተገዝቶ ሁላችንንም የይምሰል ይቅርታ የጠየቀው ቆይ እስከመቼ ነው አሹሩሩ የምንለው
አቶ ጌታቸው፡- እንደሱ ማለት እኮ አይደለም ዳዊት
ዳዊ፡- አባዬ አሁንም ጥፋቱን ለማስተባበል አትሞክር ቆይ እሺ ማታ እንዳያመሽ ካንተ ጋር ነበር የነገርነው ከእንተ ጋር ደህና እደሩ ብለህን ስትሄድ አብረን ነበርን ያቺን የእንቅልፍ ሰዓታችንን ተጠቅሞ ከተኛን በኋላ ነው የወጣው እንደዚህ አይነቱን ሱሰኛ ከቤተሰቡ መጠጥ ለሚበልጥበት ጠበቃ ልንሆን አይገባንም ቆይ ግን በእሱ የተነሳ የኛ የሁላችንም ስም እየጠፋ መሆኑን ያውቃል አንተን ነው እኮ የምጠይቅህ?
ዮሐንስ፡- ምኑን?
ዳዊት፡- ባንተ የተነሳ የሁላችንም ስም መጥፋቱን ..... መልስ ስጠኝ እንጂ ለነገሩ አንተ ምን ታደርግ የበለጠ ከብር ላንተ ይሰጥሃል እኔ እንኳን የቤቱ ታላቅ ስንቱን ነገር ችፎ ሰኖር ለሚሰቴ ያላችሁን ጥላቻ እያወኩ ለእናንተ ያለኝ ፍቅር ግን ዛሬም ትላንትም ነገም ያው ነው ይሄ እንኳን ትምህርት አይሆንህም ቆይ ግን አንተ ሃሳብህ ምንድነው ዘለለም መጠጣት ቤት መበጥበጥ በጨለማ ከቤት መውጣት መብላት መጠጣት ይሔ ነው ስራህ ይህንንማ እንስሳትም ይሰሩታል ለመሆኑ ማነው ቁልፍ የሚሰጥህ ይቺ ብርቁ ነች አይደል?
ዮሐንስ፡- እሷ ምንም አላደረገችም እሷን እዚህ ውስጥ አትከተታት ጥፋቱ የእኔ ነው እኔን ውቀሰኝ እኔ እሰማህለው
ዳዊት፡- አየኸው አይደል አባዬ እንደት መልስ እንደሚሰጠኝ ቀና ብሎ አይቶኝ የማያውቀው ልጅ ልቡን አሳብጦ <<እሰማህለው>> ይለኛል ብትሰማኝማ ተምረህ የት በደረስክ አንተ የምትሰማው የብርቁቆን ጩኸት ነው
ዮሐንስ፡- ያለመማሬንና መሃይም መሆኔን እንድትነግረኝ አልፈልግም
ዳዊት፡- ምን አልክ አንተ ሰላማችንን የምትነሳው አንሶህ አፍህን ሞልተህ ልትናገረኝ
አቶ ጌታቸው፡- ተው ዳዊት ተው
ዮሐንስ፡- አባዬ በመሃላችን አትግባ የሚፈልገውን ያድርግ እንድታውቅልኝ የምፈልገው ዶክተር የአንተን ሰላም እኔ አልነሳሁትም
ዳዊት፡- ምን ለማለት ፈልገህ ነው?
አቶ ጌታቸው፡- ኧረ ተው ዳዊት

የአለ/ት/ቤ/የ/ጠ_ገዳም_ጉሳ_ቤተ_ክርስቲያን

ዳዊት፡- ቆይ ቆይ ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
ዮሐንስ፡- ይህንን የኔ መስከር ምክንያቱ አንተ መሆንህን
ዳዊት፡- እኔ?
ዮሐንስ፡- አዎ አንተ
አቶ ጌታቸው፡- ዮሐንስ /በጥፊ ይመቱታል/ በቃህ በቃህ ብያለው
ዮሐንስ፡- ልናገርበት ልናገርበት አባ አዎ አንተ ነህ ሰላማችንን የነሳኸው እስኪ ንገረኝ እማማ ከመሞቷ በፊት እንዲ አይነት ፀባይ ነበረች አንተ የሰውን ምክር አትሰማም ሰውን ግን ትመክራለህ እንዲ ማድረግማ ቀላል ነው ለዚህ ቤት ሰላም ማጣት ትክክለኛ ምክንያት ማን እንደሆነ ታውቃለህ አንተና ገፊ ሚስትህ! ገና እግሯ ይህን ቤት ከመርገጡ እናቴ ሞተች አባቴም በሽተኛ ሆነ እኔም ቤቱ አስጠላኝ ሰካራም ቦዘኔ ባለጌ መባልን ማን ይፈልጋል?
ሶስና፡- በየሱስ ስም ምን አይነት የሰይጣን መንፈስ ነው የገባው በክርስቶስ
እመቤት፡- ምንድ ነው ነገሩ ምን ሆናችኋል?
ዳዊት፡- ምንም አልሆንም ወደ መኝታ ቤት ግቢ
ዮሐንስ፡- እንዴት ምንም አልሆንም ይነገራት እንጂ?
ሶስና፡- በየሱስ ስም ጌታዬ እዚህ ቤት የገባውን መንፈስ በስምህ ገስፀው
አቶ ጌታቸው፡- ዝም በይ አንቺ ምንም አያምርብሽም
እመቤት፡- ምንድነው የሚነገረኝ?
ዮሐንስ፡- ይሄን ነዋ ገፊ መሆንሽን ባንቺ የተነሳ ሰላም ማጣታችንን
ዳዊት፡- ተጠንቀቅ ከእሁን በኋላ አንዲት ቃል ትናገራትና
እመቤት፡- ተወው ዳዊት ንገረኝ የመጨቃጨቃችሁ ምክንያት እኔ ነኝ ምን አስቀይሜህ ነው ብመክርህ እኮ ለአንተ አስቤ ነው እንደ ልጄ ቆጥሬህ እኮ ነው
ዮሐንስ፡- አየሽው አይደል ችግርሽን ልጅሽ አድርገሽ ታስቢኝሽ የወንድሜ ሚስት እንጂ እናቴ ለመሆን አታስቢ
ዳዊት፡- ከዚህ በኋላ ሚስቴ ስትዋረድ ማየት አልፈልግም አንዲት ቃል ትናገራትና ወየውልህ የማንም ሰካራም ማላገጫ መሰለችህ
እመቤት፡- ተወው ዳዊት ውርደት አይደለም ሰክሮም አይደለም እውነት ነው የአባትህ ዝምታ ምን ይመስልሃል የቤቱን ብጥበጣ ማቆም የሚችሉ አይደለም አንድ እውነት አለ እንጂ እውነቱም እኔ ነኝ ገፊ ገደቢስ ይህን ያህል ጊዜ በጥላቻ ውስጥ ሆኜ ፍቅርን ለመስጠት ብሞክርም የቤቱን ሰላም ግን ማምጣት አልቻልኩም። እስኪ እናንተ ንገሩኝ ምን ባደርግ ነው ከዚህ ቤት ቁጥር ውስጥ የምገባው የትኛውን ሽክም ብሸክም ነው የዚህን ቤት ጥላቻ ከእኔ የማርቀው
ሶስና፡- በየሱስ ስም እኔ የምላችሁን ብትሰሙ ጥሩ ነው ጌታ የጥላቻን መንፈስ በስምህ ገስፀው በየሱስ ስም።
አቶ ጌታቸው፡- ላያምርብሽ ነገር አትቀባጥሪ
ሶስና፡- እውነት እኮ ነው አባ
ዳዊት፡- ለምን ዝም አትይም አንቺ ጉዳየ የእኛ ነው ሌላስ ምን ቀረህ ተናገራ እንሰማህ
ዮሐንስ፡- ምንም ምንም አልቀረኝም በስህተት አይን አትመልከቱኝ ተረትም አተርቱብኝ <<ሆድ ያባውን ብቅል>> አትበሉኝ ሆድ ያባውን አይደለም የልቤን ቁስል ነው የተናገርኩት።
ዳዊት፡- እንግዲያውስ ጥሩ ትሰማላችሁ አባዬም አንተም አንቺም ስሙ ሚስት በባሏ ቤት መከበር እንጂ መዋረድ የለባትም ከዚህ ከጭፍን አስተሳሰባችሁ ከወጣችሁ ጥሩ አለበለዚያ ግን ማን በዚህ ቤት መኖር እንዳለበት ማን ከዚህ ቤት መውጣት እንዳለበት አብረን እናያለን
አቶ ጌታቸው፡- ይበቃሃል ከዚህ በኋላ ማንንም መስማት አልፈልግም ማንም እኔ በሕይወት እያለው በዚህ ቤት ላይ መወሰን አይችልም።
እመቤት፡- እርስዎ ግን ይችላሉ አንድ ጥያቄ ልጠይቆት ልጅዎን መውደዴ የእኔ ጥፋት ነው እዚህ ቤት ምራት ሆኖ መገኘት ጥፋት ነው አዎ ምናልባት እድለቢስነቴ ይሆናል እኔ የዚህን ቤት ደስታ መንጠቄ ግን እኮ ሰው ሆኖ መፈጠሬ ስህተት አይደለም የዚህ ቤት ደስታና ፍቅር ለማጣት ሞክርኩ ብዙ ጊዜ ወደ እርስዎ ቀረብኩ ጠዋት ከእንቅልፌ ተነስቼ የማስበው የአናንተን ጥላቻ የማሸንፍበትን መንገድ ነው እኔ እዚህ ቤት ውስጥ ለማንም ጥላቻ የለኝም። ፍቅር እንጂ የአናታችሁም ሞት የፈጣሪ ትዕዛዝ እንጂ የእኔ አይደለም ለዚህ ቤት ሰላም ማጣት በአናንተ ዘንድ እኔ ከሆንክኝ ምን አደርጋለው እሺ ፀቅር በሉኝ እባክችሁ ደስ ከሚለው ቤተሰባችሁ ቁጥር ውስጥ አስገቡኝ ዳዊትን ባሌ ዮሐንስን ወንድሜ ሶስናን አባቴ አድርጌ አንድኖር አንድ አደል ስጡኝ ከዚህ ቤት ያጠፋውትን ሰላም መልሼ እንዳመጣው ፍቀዱልኝ እባክችሁ እባክችሁ ከዚህ ቤተሰብ አታርቁኝ /እግራቸው ላይ ተወድቃለች/
አቶ ጌታቸው፡- ተነሽ ልጂ እውነተኛ እንባ ኃይል አለው እኛን ጥፋተኛ አንቺ ምን ታደርጊ ጥላቻው ለእኛ እንጂ ላንቺ አይገባም ፀቅር በይኝ ልጂ እኔ ነኝ ጥፋተኛው ፀቅር በይኝ /እግሯ ላይ ይወድቃሉ/
ዳዊት፡- አባ ተነስ .. አንተ ገዘቅ ስትል ማየት አልወድም
አቶ ጌታቸው፡- ልጂ ልጆች ሲያጠፉ አባት ፀቅር ይላል አባት ሲያጠፉ ልጆች ደግሞ ፀቅር በሉ እግዚአብሔርም የሚወደው ይህንን ነው በእውነት ትልቅ ሰው ነሽ የነፈኩሽን ፍቅርና ትክክለኛ ቦት አሰጥሻለው።
ሶስና፡- ሃሌ ሉያ ኢየሱስ ጌታ ነው ተመስገን ጌታዬ ተመስገን ተባረክ ጌታዬ ተባረክ
አቶ ጌታቸው፡- ብርቄ ..... አንቺ ብርቄ
ብርቄ፡- አቤት አባዬ?
አቶ ጌታቸው፡- የቤቱን ሁሉ ቁልፍና ፀበል ይዘሽልኝ ነይ ያልወጣ አጋንት አለ
ብርቄ፡- እሺ አባዬ /ትወጣለች በፍጥነት ይዛ ትመጣለች/
አቶ ጌታቸው፡- /ቁልፍን ተቀብለው ለእመቤት ይሰጧታል ፀበሉን ወደ ሶስና ሲረጩ ሳለ ዮሐንስ ሆዱን ይዞ ይወድቃል ሁሉም ይጮሃሉ።

/ ዮሐንስ ላይ ተቀምጦ ምግብ ፊቱ ተደርድሮ ይታያል/
ብርቄ፡- /ምግብ ይዛ እየመጣች/ ዮሐንስ ብላ እንጂ
ዮሐንስ፡- ባክሽ ተይኝ
ብርቄ፡- ምነው አመመህ እንዴ?
ዮሐንስ፡- ሃፒታይቴ ተዘግቷል
ብርቄ፡- አዎ ዮሐንስ በቃ እኔ አጠገብህ ካልጠቀመጥኩ ሃፒታይትህ አይከፈትም?
ዮሐንስ፡- ምን ላድርግ የእኔ ኢትፍሩት ... በእኔ ምክንያት እኮ አበዋሽ ቆይ ይህን ሁሉ እኔ እንድበላው ነው ወይስ ለራስሽ ነው ያመጣሽው?
ብርቄ፡- እኔ መሰልኩ ያዘጋጀሁት እመቤት ናት
ዮሐንስ፡- ባክሽ ስሚን አትዋርቢኝ
ብርቄ፡- እንዴ ... እንደሱማ አትበል ላዛሬ አንተነትህ ስንት መከራዋን እንዳየች ታውቃለህ ዶክተሮቹ እሷን ባያውቋትና ባትጯጯዋልህ ይሔኔ ቄረሽ ነበር ይሔኔ ተስክርሽን እያወጣን ነበር ገባሽ
ዮሐንስ፡- ምነው ሞቴን ተመኘሽልኝ ይሔን ያህል አሰጠልቼሽ ነበር እንዴ?
ብርቄ፡- በስመ አብ በል አንተ ለስንቱ ታቦት እንደተሳልኩልህ እኔ ነኝ የማውቀው
ዮሐንስ፡- ለማ ለእኔ?
ብርቄ፡- አዎ ምነው?
ዮሐንስ፡- እስኪ ማርያምን በይ
ብርቄ፡- ማርያምን
ዮሐንስ- ት....ዕ....ይ....ን....ት (ፀ) /ሁ...ለ...ት.../
አለምንሽም
ብርቄ፡- ማሃላዬ እንደ አንተ መስሎህ ነው አይደል ተወው እሺ
ዮሐንስ፡- በውሸት እኮ ማርያምን ድሮ ቀረ ብርቅዬ
ብርቄ፡- እስኪ ማርያምን በል
ዮሐንስ፡- እመቤቴን ... እንደውም የሷ አዛኝነት እና ርህራሔ ነው እንጂ እኔማ ጠፍቼ ነበር
ብርቄ፡- እንዴት አንተ?
ዮሐንስ፡- አባዬ አዛኝ መሆኗን አውቀህ በስሟ የምትምለው መሃላ ዋጋ ያስከፍልሃል ይለኝ ነበር በእውነት እንደ እኔ ቢሆን ኖሮ ከሆስፒታል ባልወጣው ነበር ግን አሷ በምህረት አይኗ አየችኝ በፍቅር እጆቿም ዳሰሰችኝ ሕመሜ ወንቶ ሆስፒታል ውስጥ ሰጮኽና ሳለቅስ ልታፅናናኝ ትመጣ ነበር እኔ በስሟ ስሞሽና ስንሟድ ነቁ የብርሃን ልብስ ለብሳ ምራሃለው እያለች የሚያቃጥለኝን ቦታ ስትዳስሰኝ ሕማሜ ሁሉ ይቅመልኝ ነበር እዛው እንዳለው በሰላም ወደ ቤቴ እሸቢኝ ሰላት ትገባለህ አለችኝ ግን ብርቄ አሁን ድረስ የሚገርመኝ በየትኛው ስራዬ ነው የቀረበችኝ የትኛውን ፅድቅ ሰርቼ ነው ከሞት ያዳነችኝ እንደ እኔ ስራ እኮ ገሃነም ሲያንሰኝ ነው ስለ እውነት ብርቄ ያለ እመቤቴ የኖርኳትን የውሸት ህይወቴን አምርሬ እረገምኳት።
ብርቄ፡- አይ ዮሐንስ እመቤቴ እኮ እንደዚህ ናት የልጇን ቸርነት ይዛ ነው የምትመጣው ልጇም ቢሆን ኃጢአትን እንጂ ኃጢአተኞችን አይጠላም ከኃጢአት አንዱ ደግሞ የምታየውን ወንድምህንና አህትህን ሳትወድ እግዚአብሔርን እወድሃለው ማለት ነው።
ዮሐንስ፡- ሌላስ ምን ይላል መፅሐፍ ቅዱስ?
ብርቄ፡- <<ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ>> ይላል ባልንጀራ ማለት የምታየው የአዳምና የሄዋን ዘር ሁሉ ነው ለዚህም ጥሩ ምሳሌያችን እመቤታችን ናት ይሄውልህ ዮሐንስ እመቤታችን መላኩ ቢያበስራት ልጅ ትወልጃለሽ ሲላት እንዴት አለች ትፀንሻለሽ ሲላት ወንድ አላውቅም አለች መላኩክ ሆኖ ሊቆጣት ስላልፈለገ በምን ላሳምናት ብሎ አሰቦ ባልንጀራዋን እንደራሷ አድርጋ እንደምትወድ ያውቅ ነበርና ባልንጀራሽ /ዘመድሽ/ ኤልሳቤጥ ወንሳለች ሲላት ደስ አላትና እንደቃልህ ይሁንልኝ ብላ ወዲያ ወደ ባልንጀራዋ ቤት በፍጥነት .....
ዮሐንስ፡- /በእግራሞት እያያት/ ንገሪኝ
ብርቄ፡- የባልንጀራዋ ደስታ የእሷ ደስታ ስለሆነ ብቻ ባልንጀራዋ ነቢይ ስትወልድ የነቢዩን ጌታ ፈጣሪዋን የሁላችንን መድኃኒት ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ወለደችው
ዮሐንስ፡- ስለዚህ ባልንጀራን መውደድ በረከት አለው ማለት ነው አይደል?
ብርቄ፡- ልክ ነህ በረከት የሚገኘው ደግሞ በቀላሉ አይደለም ብዙ መስዋዕትነትን ይጠይቃል ስለዚህ ዮሐንስ እመቤት ባልንጀራህንም በዘርህ ውስጥ የደም ሃረግ ሆናለችና ሰው ምንም ይሁን ሰብአዊ ፍጥረት ነው በል በልብህ ያለውን ጥላቻ ከውስጥህ አውጣ
ዮሐንስ፡- እንዴት ይቻላል?
ብርቄ፡- <<ለሰው የማይቻል ለእግዚአብሔር ይቻላል>> ... ወይኔ ጉዴ የጣድኩትን ትቼው መጣው አውርጀው መጣውሳ /ትወጣለች/
ዮሐንስ፡- ከምትነግረኝ ውስጥ አንድም ውሸት የለበትም ደግሞ እኮ አፏ ሲጣፍጥ ለካ ለዚህ ነው ሁሌ 11 ሰዓት አይመቹኝም አያለች ነጠላ አጣፍታ የምትወጣው ወይኔ አለማወቄ ይሔኔ እኔም ብሔድ ኖሮ <<ለሰው የማይቻል ለእግዚአብሔር ይቻላል>> ይችን ማወቅ እንኳን ያቅተኝ አቤት ስንት ደከሞች አለን መሰለችሁ ስለ እግዚአብሔር ማወቅ የማንፈልግ ስለ ሃይማኖታችን ግድ የሌለን ልክ እንደ እኔ <<ሀ>> ቢሉን <<ሁ>> ማለት የማንችል የዋያቄ ምልክት ስናይ ቃለ አጋኖ የሚመስለን ለዚህ እኮነው ሰው በሰው ላይ የሚጨክነው አንዳንዴ ግን ለበጎ ነው እነዚያ ልብሴን ያስወለቁኝ ዱርዬዎች አሁን ባገኛቸው አመሰግናቸኋለው እኔ ልብሴን ባይገፉኝ ኖሮ ይሄን የመሰለ ኑሮ አላገኝም ነበር ወደድኋቸው ... ብርቄ ምን ነበር ያለችኝ ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ ይሔ አይደል እንዴ ባልንጀራን እንደራስ አድርጎ መውደድ ብርቄ ... <<ወይኔ ጉዴ ...። የጣድኩትን ትቼ መጣው አውርጀው>> ..... ወይኔ ጉዴ አበድኩ እንዴ .....ብርቄ.... ብርቄ /ይጣራል/
ብርቄ፡- አቤት ጠራኸኝ
ዮሐንስ፡- ማን እኔ?

የአባ/ቴ/ዩ/ቲ/ዩ/ብ ፕሮጀክት ጥበቃ ነው

ብርቄ፡- አዎ አሁን ብርቄ አላልከነም
ዮሐንስ፡- ኧረ አላልኩም
ብርቄ፡- ያንተን ድምፅ የሰማው መስሎኝ
ዮሐንስ፡- አይ የማርያም ብቅል እየፈጨው ነው በይ
ብርቄ፡- እንደዚያ ነው የማርያም ብቅል እየፈጨው ነው /ትወጣለች/
ዮሐንስ፡- ብርቄ
ብርቄ፡- አቤት ... የማርያምን .....
ዮሐንስ፡- አሁን እንኳን እኔ ነኝ
ብርቄ፡- አቤት
ዮሐንስ፡- ተይው በቃ
ብርቄ፡- ምን ሆነሃል ዮሐንስ?
ዮሐንስ፡- ምንም
ብርቄ፡- ለምን ጠራኸኝ?
ዮሐንስ፡- አፌ ላይ መጥቶ ነው
ብርቄ፡- የእኔ ስም?
ዮሐንስ፡- አዎ
ብርቄ፡- ዋሩ ነዋ /ወደ ውስጥ እየገባች/
ዮሐንስ፡- እንዴ ምን ሆኜ ነው በናታችሁ ..... እኔኛ እኔም አላውቀውም እ.... ብርቄ ..... ብርቄ ብርቅዬ
ብርቄ፡- ኡፍ አቤት ምን ሆነሃል?
ዮሐንስ፡- እኔ ምን አውቃለው
ብርቄ፡- ለምን ጠራኸኝ?
ዮሐንስ፡- እ.....እ .....እ ....እ
ብርቄ፡- ምን እንደ ፍየል እ...እ ትላለህ ተናገር እንጂ?
ዮሐንስ፡- ጠፋብኝ
ብርቄ፡- ምኑ?
ዮሐንስ፡- ልነግርሽ ያሰብኩት
ብርቄ፡- ፈልግና ጠብቀኝ
ዮሐንስ፡- የት ማለቴ ምኑን?
ብርቄ፡- ቁም ሳጥን ውስጥ የጠፋብህን /ልትሒድ ስትል/
ዮሐንስ፡- አገኘሁት
ብርቄ፡- ምኑን?
ዮሐንስ፡- ሞዋሚጣ ምላስሽን
ብርቄ፡- ይሔ ነበር የጠፋብህ?
ዮሐንስ፡- /በእልህ/ አዎ
ብርቄ፡- እሱ ነበር እንዴ የጠፋብህ?
ዮሐንስ፡- አዎ
ብርቄ፡- እ..... ጆኒ ለፋህ እሱን እኮ አስቀምጬልህ ነበር
ዮሐንስ፡- የት?
ብርቄ፡- የጠጅ ብርሌ ውስጥ
ዮሐንስ፡- እሺ አሁን ስድብን ምን አመጣው?
ብርቄ፡- ዮሐንስ!
ዮሐንስ፡- ውሻ በይው እሱን
ብርቄ፡- ያምሃል እንዴ እሱኮ ውሻ አይደለም
ዮሐንስ፡- ማነው እሱ?
ብርቄ፡- ዮሐንስ
ዮሐንስ፡- ምን አገባሽ አንቺ ስለ እሱ?
ብርቄ፡- ያገባኛል
ዮሐንስ፡- እሺ ያገባሻል አይ ብርቄ ውሻ ማለት እኮ ለጌታው አገልጋይ ታማኝ ማለት ነው
ብርቄ፡- አይደለም ውሻ ማለት ወደ ትፋቱ የሚመለስ መናፍቅ ማለት ነው
ሶስና፡- እንደምን አደራችሁ?
ዮሐንስ፡- አሁን ስላንቺ ስናወራ መጣሽ
ሶስና፡- ስለእኔ በጌታ ስም እንዴት ደስ ይላል
ዮሐንስ፡- አዎ ወደ ትፋቱ የሚመለስ .....
ሶስና፡- ስለ ያም ልታወራብኝ እንዳይሆን

ብርቄ፡- አባዬ በጣም ተቆጥቷል እስከ ምሽቱ ሰባት ሰዓት ሲጠብቅሽ ነበር
ዮሐንስ፡- ቆይ ቆይ ኧረ የት ነው ያደርሽው?
ሶስና፡- ከጌታ ጋር በልዩ አምልኮ አቤት የዛሬዋ ቀን መንፈስ ቅዱስ ከሰማይ ወርዶ በሁሉም አምላኪዎች ላይ በቃ ጌታን ስናመልክ አመሸን
ዮሐንስ፡- የእኔ ጥያቄ እኮ የት አመሸሽ አይደለም የት ነው የደርሽው ነው
ሶስና፡- ዋው ድንቅ ነገር ነው የጌታ መንፈስ ያደረበት አንድ አገልጋያችን ሰው በህልሜ ጌታ ካንቺ ጋር እንዳድር ነገረኝ አለኝ እንዴት ያለህ የመንፈስ ሰው መሰለህ አጋንት ሲያወጣ ልሳን ሲናገር ትንቢት ሲናገር በየሱስ ስም
ብርቄ፡- የጌታ መንፈስ አመንዝሩ ይላል እንዴ
ሶስና፡- ፀጋ ነዋ ጳውሎስ ምን አለ መሰለሽ ለእያንዳንዳችን የተለያየ ፀጋ አለን መጸለይ፣ በልሳን መናገር፣ በህልም መገለጥ ለእርሱ ግን ቢያንስ ሶስት ፀጋ አለው በልሳን ይናገራል፣ በህልሙ ይገለጥለታል፣ ዝማሬውንማ አታንሽብኝ እሱ ሲዘምር ሰው ሁሉ በተመስጦ ሃሌ ሉያ .....
ዮሐንስ፡- ይሔን ቱሪናፋሽን ፋዘር እንዳይሰማሽ ቆይ አንቺ ግን አእምሮ የለሽም ማገናዘብ አትችይም እንዴ ደግሞ አፏን ከፍታ <<በህልሜ ጌታ ካንቺ ጋር አደሪ ሲለኝ>> አደርኩ ማፈሪያ እኔ ማሃይሙ እንኳን ዝሙት ኃጢአት መሆኑን አውቃለው
ሶስና፡- ዝሙት እኮ አይደለም የጌታ ፈቃድ
ዮሐንስ፡- የጌታ ፈቃድ ትዕዛዙን እንድንጠብቅ ነው ከትዕዛዛቱ አንዱ ደግሞ አታመንዝር ነው
ሶስና፡- አልበራላችሁማ .... ለእዚ ነው እነኮ አምልኮ የማታውቁት የጌታን ፈቃድ የማታስተውድት ጌታ ሆይ በዚህ ቤት መንፈስህን አውርድ ትሰማላችሁ የባርነት ዘመን ቀርቷል ዘመኑ የሃርነት ነው በየሱስ ስም ነፃ ወጥተናል ስለዚህ የት ገባሽ የት ወጣሽ ምናምን የባርነት ዘመን አልፏል እሺ
ዮሐንስ፡- እሺ የሚመጣውንም አብረን እናያለን
ሶስና፡- ምን ትገተራያለሽ የሚበላ አምጪ እንጂ ..... አንቺን እኮ ነው
ዮሐንስ፡- ቀስ ሲሰቱ ቀስ /ብርቄ ወደ ወስጥ ትገባለች/
ሶስና፡- መቀርቀርህ ነው እንዴ?
ዮሐንስ፡- አዎ መቀርቀሬ ነው ለነገርማ አንደኛ ነሽ
ሶስና፡- በየሱስ ስም ምነው እንደዚህ አንጨረጨረህ የተናገርኳት ሰራተኛዋን
ዮሐንስ፡- ሠራተኛ ሠራተኛማ አይደለችም
ሶስና፡- እና ምንድናት?
ዮሐንስ፡- አባዬ እንዳይሰማሽ
ሶስና፡- የአባዬ አቃጣሪ አንተ ሰማህ አይደል ሒድና አቃዋርለት
ዮሐንስ፡- እንዴ አንቺ ግን ምንድ ነው ያጠገበሽ
ሶስና፡- ቀርሰህ፣ አርሰህ ያበላኸኝ መሰለህ እንዴ ልታዘኝና ልትገስፀኝ አትሞክር እንደ ተናሽነትህ ተግባባን
ዮሐንስ፡- አዎ ተግባባን ግን እንድታውቂ የምፈልገው ብርቄ የቤተሳኝን አባል መሆኗል ነው
ሶስና፡- ማነው አባል ያደረጋት አንተ?
ዮሐንስ፡- የቤቱ ኦነር
ሶስና፡- አንተ?
ዮሐንስ፡- አባዬ የአባት ትዕዛዝ ደግሞ መክበር አለበት
ብርቄ፡- /ምግብ ይዛ እየጋባች/ ምንድ ነው የሚያጨቃጭቃችሁ?
ሶስና፡- አምጪው ምግቡን
ዮሐንስ፡- አንቺ ልጅ ያምሻል እንዴ
ሶስና፡- አንተ ልጅ ያምሃል እንዴ ልብላበት አትልክፈኝ /አይኗን ጨፍና ትስጸልይ ምግቡን አንስቶ ይበላባታል/
ዮሐንስ፡- /አየበሳ/ ግን ሶሲ ጌታ ሲጸልይ አይኑን ወደ ላይ አንስቶ ነው አይደል?
ሶስና፡- በምን አወክ በጌታ ዘመን ነበርክ እንዴ?
ዮሐንስ፡- የሰራችሁትን ፊልም አይቼ
ሶስና፡- ጥያቄህ ገባኝ ለምን ጨፍንሽ ትጸልያለሽ ለማለት ነው አይደል? ሃሳቤ እንዳይበታተን ነው ጸሎተ ደግሞ ስትጨፍን በደንብ ከጌታ ጋር ትገናኛለህ
ብርቄ፡- አባታችን ሆይ ሰንል አይናችን አብሮ የአባትነት ፍቅሩን ያያል በሰማይ የምትኖር ሰንል ደግሞ አይናችን ወደ ሠማይ እንጂ መጨፈን ያለብን አይመስለኝም።።
ሶስና፡- የእኛ አስተማሪ ማነው እንዲ የሰበከሽ?
ብርቄ፡- መፅሐፍ ቅዱስ
ሶስና፡- መፅሐፍ ቅዱስ እንዲ ይላል?
ብርቄ፡- በሚገባ
ሶስና፡- ምን ላይ እስኪ አሳይኝ?
ዮሐንስ፡- ኧረ በደንብ ይላል
ሶስና፡- እኮ ምን ላይ /መፅሐፍ ቅዱስ ተቀብሏት ያገለባብጣል/
ሶስና፡- እየሳቀች ኧረ ገልብጠከዋል አስተካክለውና ያዘው /ግራ ተጋብቶ ገጾችን ይገልባል/
ዮሐንስ፡- /ወደ ብርቄ ጠጋ ብሎ/ ይላል አይደል ብርቄ?
ብርቄ፡- አዎ
ዮሐንስ፡- ይሔው ይላል የባልጀራውንም፣ የውሻውንም የትፋቱንም በደንብ ንገሪያት
ብርቄ፡- ለምሳሌ በመጽሐፈ መሳሌ ምዕራፍ ***16:30*** ላይ <<አይኑን የሚዘጋ ጠማማ ሃሳብ ያስባል>> ይላል

ት.....ዕ.....ይ.....ን.....ት (ፎ) /ሥ...ለ...ት.../

ዮሐንስ፦ የበለስ ምግብ ላይ ምን
ጠማማ ሃሳብ አሳስበኝ እያየሁት መብላት ነው እንጂ የእኔ እናት
ሶስና፦ ጠማሞች መቼ ነው ግን አንቺ እንደዚህ ሙጢ የሆንሺው?
ዮሐንስ፦ እራት አብራን የባላች ለት
ሶስና፦ ምን አልክ?
ዮሐንስ፦ በር ይንኳኳል
ሶስና፦ ሒጂ ከፊቴ
ዮሐንስ፦ እኔ አከፍታለው
ሶስና፦ እሷ እያለች?
ዮሐንስ፦ አዎ እሷ እያለች
ሶስና፦ ለምን?
ዮሐንስ፦ የጨፈንሽው አይን እንዲገለጥ ..... ስትገልጪው ንገሪኝ
ሶስና፦ ምላስ ስትጎርሱ ነበር እንዴ
ብርቄ፦ የእግዚአብሔር ቃል ምላሰን ያንቀሳቅሳል እንደበትንም በስርዓት ያከናውናል
ሶስና፦ ምን አልሽ አንቺ መፅሐፍ ቅዱስን ልታስተምሪኝ?
ብርቄ፦ <<እግዚአብሔር የሰለም አምላክ እንጂ የሁከት አምላክ አይደለም>>
ሶስና፦ እና እኔ ሁከተኛ ነኝ አንቺን እኮ ነው የምልሽ?
ብርቄ፦ እኔ እንደዚህ አላልኩም
ሶስና፦ እና ምን ማለትሽ ነው አሀ ....<<ውሻ ምናምን>> እያለ ለካ እኔን ነው ማነው ውሻ አንቺ አንቺን እኮ ነው?
አቶ ጌታቸው፦ ምን ልታደርጊ ነው?
ዮሐንስ፦ ቆይ ተረጋጊ ሃሌ ሉያ
እመቤት፦ ምነው ሶሲ
ሶስና፦ በቤቴ ትሰድበኛለች እንደ
ዮሐንስ፦ መሳደብ ልማዷ አይደለም
አቶ ጌታቸው፦ እንዴ አንቺ ልጅ ምን አድርጉ ነው የምትሏት አቅም ያለውም የሌለውም ምነው አሷ ላይ በረታ ቆይ የእኔን ትዕዛዝ አትሰሙም ማለት ነው እኔ ነግሬያለው ይኽን ልጅ ካሁን በኋላ በአፋም ሆነ በዓይኑ አንድ ሰው ቢናገራት ወሮለት
እመቤት፦ አባዬ እውነቱን ነው ቤታችን የሰላም የፍቅር ቤት መሆን አለበት ስለዚህ ሁላችንም በመተሳሰብ ችግር ካለ በመነጋገር የዚህን ቤት ሰላም ለዘላለም መጠበቅ አለብን እንጂ እንደዚማ ጥሩ አይደለም
ሶስና፦ እና በሠራተኛ ተዋ..... ርጂ
አቶ ጌታቸው፦ ዝም በይ አንቺ ስራ ያሳጣሽ የትም እያደርሽ ጋኔን ይዘሽ ትመጪያለሽ
እመቤት፦ አባዬ ብዙ መናደድ ለጤናህ ጥሩ አይደለም ጉዳዩን ለእኔ ተውልኝ እኔ አስታርቃቸዋለው እርግጠኛ ነኝ እኔ የምላቸውን ይሰማሉ ሒድ ግባና አረፍ በል
አቶ ጌታቸው፦ ቆይ እመቤት የት እንዳደረች ሃሳቧ ምን እንደሆነ ትንገረኝ ለመሆኑ የት ምን እየሰራሽ ነው ያደርሽው?
ዮሐንስ፦ ህልም እውን ስታደርግ
ሶስና፦ ክብር የማይወድልህ ከሆነ ማንንትህን እነግርሃለሁ ትሰማለህ አባዬ የፈለኩትን የማምለክ መብት አለኝ
አቶ ጌታቸው፦ የማደር ግን የለሽም ከሃይማኖትሽ መች ሆነና ጥሌ የእኔ ጥል ማደር ከሚሉት ነው እንጂ ልብ አርጊ አንቺ ልጅ በተከበርኩበት አከባቢ ባንቺ የተነሳ መዋረድ አልፈልግም ይሒ ልደር ልደር ሆድ ለማሳበጥ ነው
ሶስና፦ እኔ እራሴን የማላውቅ ሀፃን ለጅ አይደለውም በጌታ ፊቃድ በፍቅሩ የተጠራው ምርጥ አገልጋይ ነኝ
ዮሐንስ፦ አገልግል በይ እንጂ
ሶስና፦ አባዬ ግን ይሒን ልጅ አሳርፈው እኔ የሱን ሃይማኖት ነቅፈአለው እሱን ተናግሬዋለው
ዮሐንስ፦ ምን ታስባኪያለሽ መብራት ሃይል ምን ምን አንዴ በራልኝ አንዴ ጠፋብኝ ቆጣሪ አስገጥመሽ ነው አንዴ የምትዘረው
እመቤት፦ ተው ዮሐንስ እንደ እሱ አይደለም ሶስናም ተረጋጊ የቤታችንን ጉዳይ አብረን እንፍታው ሰው በራሱ ከዙር ፍጡር ነው ስለዚህ የሁላችንንም አይን ሁሉንም እኩል ማየት አለበት ድሃ ሃብታም ትንሽ ትልቅ የተማረ ያልተማረ ማበላለጥ የለብንም ለእግዚአብሔር ሁላችንም እኩል ነን የማናችንን ሚዛን ይመዝናል የማናችን ዕድት ሚዛን ይደፋል እርሱ እንደ ስራችን ነው እርግጠኛ ሆኜ የምናገረው ከአንድ ክርክር በስተጀርባ አንድ አላዋቂነት አለ በእንደዚህ ሁኔታዎች ስለ ሃይማኖትም ስለቤተሰብም ባጠቃላይ ስለ ሰላም ማውራት አንችልም አሁን ነገሮችን እናቅላቸውና ጉዳዩን በይደር እንየው በቀዝቃዛ አእምሮ የሁላችንንም ጥያቄ እንመዝንዋለን አይመስላችሁም?
ሶስና፦ ጥሩ የእኔም የእንቅልፍ ሰዓቴ ደርሷል ሌላ ጊዜ በደንብ እናናዋለን
እመቤት፦ ብርቄ አንቺም ቢሆን ገለልተኝነት አይሰማሽ የቤተሰባችን አንዷ አባል አይደለሽም እንዴ?
ብርቄ፦ ጥሩ አሰባችኋል እኔ ግን ለዚህ ክብር የማልበቃ ነበርኩ አጥፍቼም ከሆን ይቅር በሎኝ ሌላ ምንም የምናገረው የለም
አቶ ጌታቸው፦ አያችሁ አይደል ትልቅነት ክርስትና ይሒ ነው ተበዳይ ሆኖ ይቅር በሎኝ የሚል ብርቄ እግዚአብሔር ይሰጥሽ /ይባርክሽ/
ብርቄ፦ አሜን አባዬ
አቶ ጌታቸው፦ ደሜ ባትሆኝም ውስጤ ግን ደምህ ነኝ ይለኛል እግዚአብሔር ምስክሬ ነው ከልጆቼ አሳንሼ አላዩሽም
ዮሐንስ፦ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲ ይላል <<ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ>> ደግሞም <<የምታያቸውን አህትና ወንድሞች ያልወደደክ የማታየውን እግዚአብሔርን አወደዋለው ማለት ውሸት ነው>> ይለናል ስለዚህ እንኳን አጠገባችን ያለውን ማንኛውንም ሰው የመውደድ ሃላፊነት አለብን አይደል እንዴ ብርቄ?
አቶ ጌታቸው፦ በሉ አሁን እኔም ስለደከመኝ አረፍ ልበል ይሒን የሰላም መንፈስ መልሳችሁ አታደፍርሱት
እመቤት፦ ዮሐንስ ይሒ የአስተማሪነት መንፈስ ከውስጥህ እንዳይወጣ ለካ ብዙ መማር አንችል ነበር ካንተ ሰላም፣ ጦርነትም፣ ይቅርታም ምህረትም አለ አንተ ከቤት ስትርቅ ግን ቤቱ ሁሉ ጭር ይላል ያንተ መታመም ቤቱን ምጥ ውስጥ ከቶት ነበር ተመስገን አሁን በቤታችን ላይ ነግሶ የነበረው ማዕበል ጸጥ ብሏል።
ዮሐንስ፦ እኔንቴ ተፈትኖበታል በተለይ መሃላዬ ወንቷል ማርያምን ግን ያልገባኝ ነገር የመታመሜ መነሻ ምንድ ነው?
አቶ ጌታቸው፦ የምግብ መመረዝ ነው አሉ
ዮሐንስ፦ የምግብ መመረዝ እንዴት?
አቶ ጌታቸው፦ እኔ ምን አውቃለው ገብሱ አይቀርህ ማሩ አይቀርህ በቀሎው አይቀርህ ጤፍ፣ ሽሮ ምን የእህል ዘር ይቀራሃል አንተ በወፍራሙም በቀጪኑም በሚበላውም በሚጠጣውም ታገኝዋለህ
ዮሐንስ፦ አይ አባዬ እኔ እኮ ምንም ነገር የማላውቅ ምስኪን የአብርሃም በግ ነኝ
አቶ ጌታቸው፦ መች ጠፋኝ ልጂ እንደው የይስሃቅ ዶሮ መሆንህ ገርሞኝ ነው እንጂ
ብርቄ፦ እኔ ግን ዶክተሮቹ የተሳሳቱ ይመስለኛል
ዮሐንስ፦ እንዴት የእኛ ፕሮፌሰር?
ብርቄ፦ ምን አልባት የመጠጥ መበከል እንዳይሆን
/ሁሉም ይሰቃሉ ዮሐንስ እንደ መታመም ሲል ሁሉም ይጯጯሀሉ ይስቅባቸዋል ውሸት መሆኑን ሲያውቁ ሁሉም እጃቸውን ያሳርፉበታል መብራት ይጠፋል።

እመቤት፦ አባዬ ዛሬም እንቅልፍ እንቢ አለህ እንዴ?
አቶ ጌታቸው፦ አይ ልጅ ወትሮስ በዚህ ሰዓት መች አተኛለሁ
እመቤት፦ ግን እኮ ጠዋት የምትነሳ ከሆነ ኤክሰርሳይሱን ብትጀምር ለጤንነተህ አረፍ ነው?
አቶ ጌታቸው፦ ኧረ ሰው ምን ይላል መሳለቂያ ነው የሚያደርገኝ ባይሆን እንደ ትላንቱ ሰንበትን እየጠበኩ እሮጣለው እንጂ የሁል ጊዜውስ ያስፈራኛል
እመቤት፦ ስለ ጤንነትህ እንጂ ስለ ሰው ብዙም አትጨነቅ ደግሞ እኮ ብቻክን አትሆንም እኔም አለው ብዙ አባቶችም በሠንበት ብቻ ሳይሆን በአዘቦት ቀንም ይሮጣሉ
አቶ ጌታቸው፦ አይ የእኔ ልጅ አሁንም መሮጥ የምችል ይመስልሻል?
እመቤት፦ እንዴት አባዬ?
አቶ ጌታቸው፦ እግሬና ሰውነቴ ሁሉ ተሳስሯል ቤተ-ክርስትያን እራሱ መሒድ ፈልጌ ነበር
እመቤት፦ እስትራፆ ነው ይሰቅሃል አባዬ ..... በል ይችን ወተት ጠጣ ላንተ ነው ያዘጋጀሁት
አቶ ጌታቸው፦ /ተቀብለው ሊጠጡ ሲሉ/
ብርቄ፦ /እየቀማቻቸው/ ዛሬ እኮ ያም ነው ምነው በጠዋቱ
እመቤት፦ ዛሬ ደግሞ ያምን ምን አመጣው?
ብርቄ፦ እንዴ ዛሬማ ሀፃን የለ አዋቂ የለ ላም የለ በሬ የለ ሁሉም የሚያሙት ነገሜ ነው እንግዲ አባዬ ለሶስት ቀን መበርታት ነው
አቶ ጌታቸው፦ ውይ ..ውይ ለካ ቅር የሚለኝ ለዚህ ነው በይ ብርቅዬ ጋ ቢዬን አምጪውልኝ /ወደ ውስጥ ትገባለች/
ዳዊት፦ ደህና አደራችሁ አባዬ?
አቶ ጌታቸው፦ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና አደርክ ዳዊት?
ዳዊት፦ አይ አባዬ አሁን አሁንማ ባንተ ቀናው
አቶ ጌታቸው፦ ለምን አንተ?
ዳዊት፦ ሚስቴ እኔን ማገልገል ትታለች ጠዋት ስነሳ እንኳን አጠገቤ አላገኛትም
አቶ ጌታቸው፦ ምነው አንተ ቀናህ እንዴ እንግዲ አባት መሆኔ ቀረ እንዴ?
ዳዊት፦ ምናለ ለእኔም አንዳንዴ ወተት ወይንም ጁስ ብታመጪልኝ?
እመቤት፦ ቃልህን አትርሳ እንጂ
ዳዊት፦ የምን ቃል እሙ?
እመቤት፦ አባዬን ተንከባከቢው የሁላችንም ፍላጎት ይሒ ነው ስትል አልነበረም?
ዳዊት፦ ከእኔ የሚያርቅሽ አልመሰለኝ ነበር

ብርቄ፡- ጋሼ ደህና አደርክ?
ዳዊት፡- ደህና አደርሽ ብርቄ ገሽ እንኳን መጣሽ የሚበላ እንዴት እርቦኛል መሰለሽ
ብርቄ፡- አይ ጋሼ
ዳዊት፡- ምነው ብርቄ?
ብርቄ፡- እንግዲ ቻል አድርገው
ዳዊት፡- እንዴት?
ብረቄ፡- ነሳዊ ነች
ዳዊት፡- ውይ ብርቄ ቁርስ የለም እንዳትይኝ?
ብርቄ፡- ሰው የለ እንሰሳ የለ .....
ዳዊት፡- በቃ በቃ እሙ ዛሬ እረፍት ነሽ መሰለኝ አባዬ እንግዲ ጠዋት ተነስቼ እንደ እሙ ባላገለግልህም አካሔድህ ወደ ቤተ-ክርስትያን መሰለኝ በመኪና ልሸኝህ በዛውም /ሀዱን አያሻሽ/
አቶ ጌታቸው፡- እንዴት ያለች ልጅ መሰለችህ እመቤት በስህተት ቦታዋን አሳዋቻት ነበር ብሩክ የሆነች ልጅ ለእኔ የሚገባውን ሁሉ እሷ ታውቃለች በል እንሒድ /ተያይዘው ይወጣሉ ብርቄም ወደ ውስጥ ትገባለች/
እመቤት፡- /እንድ ዱላ ይዛ መሬት ስትቀመጥ እናያታለን በመንፈስ ትጨፈነቃለች/
እመቤት፡- አሁን ሁሉም ነገር ተስተካክለሏል ካሁን በኋላ ያየዋትን መከራ ያለቅስኳትን እንባ አያንዳንጁን ያከፍሏታል ግን አሁን አቶ ጌታቸውን በሆነ ነገር በመድኃኒት ብገላቸው እድሜ ገደላቸው እንጂ እመቤት የሚል የለም ልክ ነኝ አዎ ልክ ነኝ እንጂ ማነሽ አንቺ ብርቄ
ብርቄ፡- አቤት
እመቤት፡- ሶስናን ቀስቅሻት
ብርቄ፡ ኧረ እኔ ከፍሏ አልገባም
እመቤት፡- ለምንድነው የማትገቢው?
ብርቄ፡- እሷ ማንም ከፍሏ ውስጥ እንዲገባ አትፈልግም
እመቤት፡- ትዕዛዜን አላከብርም ነው እንዴ?
ብርቄ፡- ኧረ እኔ አልወጣኝም /ወደ ውስጥ ትገባለች/
እመቤት፡- /እንደ ማሰብ አያለች/ ብርቄ .... አንቺ ብርቄ
ብርቄ፡- አቤት
እመቤት፡- ምን አለችሽ?
ብርቄ፡- ኧረ እኔ አልቀሰቀስኳትም
እመቤት፡- እና እስከ አሁን ምን እያደረግሽ ነው .... ምን ታፈጪያለሽ አንቺን እኮ ነው?
ብርቄ፡- በስመ አብ ዛሬ ደግሞ በጠዋቱ ምን ሆንሽ
እመቤት፡- ልትሰድቢኝ ነው እንዴ?
ብርቄ፡- ኧረ እኔ ቅሌታም አይደውም
እመቤት፡- ማነው ቅሌታም አንቺ..... እንዲንቅና እመቤት አልታዘዝ ማለትሽ አንሶ ትሰድቢኛለሽ እንዴ ውይ ሶስና እንኳን መጣሽ ቅሌታም አለችኝ እኮ
ሶስና፡- ምንድ ነው እሱ?
እመቤት፡- ሰደበችኝ እኮ ነው የምልሽ
ሶስና:- አንቺ የዚህ ቤት ሃላፊነት ያለባትን ነው የምትሰድቢያት?
ብርቄ፡- ኧረ እኔ አልተሳደብኩም
ሶስና፡- ዝም በይ አንቺ ለማያውቁሽ ታጠኚ ለዮሐንስ የጣፈጠ የላመ እያበላሽ ላንቺ እንዲቆረቆር አደረግሽው እኔ ግን ከብሬን በወጥ የምለውጥ ኢሳው አይደለውም ገባሽ ኧረ ቆይ ትላንት መካሪና ታዛዥ አልነበርሽ ታዲያ እንዴት ብታብጪ ነው በይ ዞር በይ ከፊቴ
ብርቄ፡- /እያማተበች ወደ ውስጥ ትገባለች/
ሶስና:- ይቺ ለካፊ በጠዋት ምን አድርጊ ነው የምትልሽ?
እመቤት፡- ባንቺ የተነሳ ነዋ
ሶስና፡- በእኔ የተናሳ! ምን?
እመቤት፡- ትላንት ለዛሬ የሆነ ቦታ እንሒድ እረፍት ነሽ ሆይ ስልሽ ቸርች ጉዳይ አለኝ አላልሽኝም?
ሶስና፡- ብዬሻለው
እመቤት፡- በቃ እንዳይረፍድብሽ ቀስቅሻት ስላት ምን እንዳችኝ ታውቂያለሽ?
ሶስና፡- ምን አለችሽ?
እመቤት፡- ማታ ያስገባችው ጎረምሳ ብደበድበኝስ
ሶስና፡- ጎረምሳ!
እመቤት፡- ከየት እንዳመጣችው ቃሉን አላውቅም
ሶስና፡- አንቺ ብርቄ እንዴት ነው የጠገበችው በጌታ ..... የምን አባሽ ጎረምሳ ነው አንቺ ..... ቤተሰብ ነሽ ስትባይ ጭንቅላቴ ላይ መውጣት አማረሽ
እመቤት፡- እይው ጥጋቧን እንዴት ደረቷን ነፍታ እንደምታይሽ
ብርቄ፡- ያበላችሁኝ አይመስለኝም ..... ነገሩን በልክ አድርጉት
ሶስና፡- በየሱስ ስም ምን አይነት ጥጋበኛ ነሽ ባክሽ ቄራሽ የቤቱ አዛዥ መሆን አማረሽ <<ያበላሽኝ አይመስለኝም>> እና የማንን እንጀራ ነው የምትበይው ጋሼ የሚያመጣውን አይደል የእመቤት ማለት ነው ገባሽ አሃ አሁን ገና ገባኝ አንቺ ሃላብሽ የአባቴን ጥላቻ ተመርኩዘሽ በዚያ ዲቃላ ምክንያት የቤቱ አዛዥ ለመሆን ነው አይደል ቆይ ምን ማድረግ እንዳለብኝ እኔ አውቃለው እንዴ ለዮሐንስ የምትቆረቆረው ወይሽ አይደለም
ብርቄ፡- በቃችሁ ዝምታዬን ፍራቻ አታድርጉት
እመቤት፡- ነይ ደብዳቤና እሱ ነው የቀራሽ
ብርቄ፡- አቅሜን የማውቅ ነኝ ..... አብድም አይደለሁም
እመቤት፡- ታዲያ እኛነን አብድ ..... እንዴ አብዳችኋል እኮ ነው የምትለን ሰማሻት
ሶስና፡- አብድ በቤቴ አብድ ትይኛለሽ ይምጣ ብቻ አባዬ ዛሬ ወዩ እኔ ወይ አንቺ እዚህ ቤት እንዴት ነው የጠገበችው በእናታችሁ
ብርቄ፡- ምንድነው ውስጣችሁን ያደፈረሰው ለምን ረጋ ብለን አንነጋገርም
እመቤት፡- ምን ስጠጣ አየሽት የደፈረሰ ምናምን የምትይው ትሰሚያለሽ ሶስና ሰካራም እኮ ነው የምትልሽ
ሶስና፡- ምናባሽ ስጠጣ አየሽኝ አንቺ ለምትጠጡት ለእናንተ የማገዛን ነኝ እሺ ውጪሊኝ ከፊቴ
ብርቄ፡- /ትወጣለች/
ሶስና፡- እንዴ ..... እንዴ ....እንዴ ዋጋብ
እመቤት፡- ያ ዮሐንስ ተብዬ ነዋ ያጠገባት የተለየ ጸባይ ነው ያለው
ሶስና፡- የማንም ውዳቂ መሰብሰቢያ አደረገው ቤቱን አባዬ
እመቤት፡- ውዳቂ! ማነው ውዳቂ?
ሶስና፡- ይሔ ዮሐንስ ተብዬ ነዋ ማንነቱን የማያውቅ ወፍ ዘራሽ
እመቤት፡- እ... <<ማንነቱን የማያውቅ>> ወምድምሽ አይደል እንዴ?
ሶስና፡- ወይኔ ጉዴ! ይህንን ጉዳይ ለማንም እንዳትነግራብኝ እሺ እራሱ ዮሐንስም አያውቅም ቃል ግቢልኝ ይሔንን ነገር ለማንም እንዳትነግሪ
እመቤት፡- አልናገርም ግን የሐንስ የዚህ ቤት ልጅ አይደለም?
ሶስና፡- አውነቱ አሁን የምነግርሽ ነው የአባቴ የጓደኛው ልጅ ነው ገና ህፃን እያለ ነው ሳይፈልጉ የተገኘው አባትዬው የእኔ አይደለም ይል ነበር እናቱ ነች በጠዋት በአባቱ በር ላይ ጥላው የሔደችው ይባላል ይህንን ነገር ለማወቅ አባዬን ስጠይቀው አይነግረኝም ምክንያቱ ደግሞ አባቱ የሞቱት በዚህ ቤዝ ይመስለኛል
እመቤት የእኛ አክል ስለሆንሽ ነው ይህንን የምነግርሽ ለማንም አትናገሪ
እመቤት፡- ኧረ ለማን ይነገራል ሆድ ይፍጀው እንጂ ሶሲ
ሶስና፡- /ሳታስበው ወደ ላይ ይላታል/
እመቤት፡- ምን ሆነሻል ሶሲ?
ሶስና፡- አይ ምንም ዝም ብሎ ያቅለሸልሸኛል
እመቤት፡- አዲስ ነገር ነው ወይስ የቆየ
ሶስና፡- ኧረ ዛሬ ሌሊት ነው የጀመረኝ እንዲሁ ሲያስመልሰኝና ሲያቅለሸልሸኝ ነው ያደረው
እመቤት፡- ታዲያ ምን ተሻለ ሐኪም ቤት ልውሰድሽ
ሶስና፡- አይ ከፖስተር ዳንኤል ጋር የጸሎት ፕሮግራም አለኝ
እመቤት፡- አብረን እንውጣ እኔም ዳዊት ቢሮ መሔድ እፈልጋለው
ሶስና፡- እሺ መጣው ልብሴን ቀይሬ /ትወጣለች/
እመቤት፡- አሁን ልቤ ሊረበርስ ነው ሶስናም አርግዛለች አባቷ ይህን ሲሰሙ በደም ብዛት ወይ ይሞታሉ ወይ ፓራላይዝ ወንድሟ ወፍ ዘራሽ መሆኑን ሲያውቅ ቤቱን ጥሎ ይሔዳል ብርቄም ትፈንገላለች ቤቱም ሃብቱም ንብረቱም የሚሌ ዳዊትም ቢሆን ትንሽ ቆይቶ ይፈነገላል እንደዚያ እንዳሰስለቀሱኝ ባሰስለቅሳቸው ሞቼአለው በዚህ ቤት ውስጥ የማይጠፋ እሳት ነው የማነደው አሁን ልዘጋጅና ልሒድ
ብርቄ፡- ምን አይነት የተመሳሰሰ ጉዳይ ነው ባካችሁ አሁን እኔ ምንድነው የማደርገው ወይኔ ዮሐንስ የማትችለውን ሸክም ነው የምትሸከመው አምላኬ ፅኑ ጉልበት ስጠው እመቤቴ አደራሽን
ሶስና፡- አንቺ ቆይ..... አሰራልሻለው ትንሽ ጠብቂኝ እሺ እመቤት ጨርሻለው ውጪ /ተያይዘው ይወጣሉ/
ብርቄ፡- ልንገረው አይ ጥሩ አይደለም ሰላሙን ያጣል ቀላል ነገር አይደለም ምስኪን ዮሐንስ .... አባዬ ግን .... አይ በእሱ ላይም አይፈረድም እኔም በእሱ ቦታ ብሆን እንደውም ጥሩ ነገር ነው ያደረገው በአሁኑ ዘመን ማን እንደዚህ ያደርጋል /በሃሳብ ትንጉዳለች/
ዮሐንስ፡- ብርቄ የእኔ ቆንጆ
ብርቄ፡- መጣህ እንዴ?
ዮሐንስ፡- አቤት ዛሬ ኪዳን ላይ የተማርነው ትምህርት እንዴት ይጥማል መሰለሽ ትምህርት አ... አ አዳም ሔዋንን ሕይወቴ ይላት ነበር አለ ቆይ ቆይ ቆይ እኔ ግን አንቺን ምንድ ነው የምልሽ ብርቅዬ
ብርቄ፡- ብርቄ
ዮሐንስ፡- አይ ማሉቴ .... ተይው በቃ ..... ቆይ ግን ምን ሆነሻል ዛሬ ልከ አይደለሽም?
ብርቄ፡- አይ ደህና ነኝ
ዮሐንስ፡- ምን ሆነሻል ንገሪኝ?
ብርቄ፡- ምንም አልሆንኩም
ዮሐንስ፡- እመቤቴን በይ እስኪ
ብርቄ፡- ምንም አልሆንኩም አልኩህ
ዮሐንስ፡- ታዲያ ምነው ተቆጣሽ ብርቄ የሆነ ነገርማ አለ ከእኔ የደበቅሽው ምንድ ነው እሱ?
ብርቄ፡- አይ ምንም ..... ማንም ግን ..... እንደባዳ ሲያይህ ደስ አይልኝም

ዮሐንስ፦ የተናገረሽ ሰው አለ እንዴ?
ብርቄ፦ አይ ግን እንዲሁ አዚህ ቤት ክብር እየተሰጠህ አይደለም
ዮሐንስ፦ ክብር ከስራ እንጂ ከሰው መጠበቅ ከንቱ ነው አይደል አንድ ነገር ልጠይቅሽ
ብርቄ፦ /ቁንቅላቷን ታወዛውዛለች/
ዮሐንስ፦ ልንገራት እንዴ ቆይ ግን ብርቄ እኔ ግን ላንቺ ምንሽ ነኝ
ብርቄ፦ ባልንጀራዬ
ዮሐንስ፦ ባልጀራ ..... እና የዛንለት ባልንጀራህን ውደድ ያልሽኝ ቆይ እኔ አንቺን እንደራሴ መውደድ አለብኝ?
ብርቄ፦ ወደህ ነው
ዮሐንስ፦ እና እኔ አንችን መውደድ አለብኝ?
ብርቄ፦ ግድ የለም ጥላኝ
ዮሐንስ፦ ኧረ ጠላትሽኝ እኔማ እወድሻለው
ብርቄ፦ ምን አልክ ?
ዮሐንስ፦ አሁን የሰማሽውን
ብርቄ፦ አልሰማውህም ድገመው?
ዮሐንስ፦ አትዋሺ ሰምተሻል
ብርቄ፦ አልሰማውህም አልኩህ
ዮሐንስ፦ ምን ሰል?
ብርቄ፦ አወድሻለው ስትል /ታፍራለች/
ዮሐንስ፦ አንቺ ግን ትወጅኛለሽ?
ብርቄ፦ ጠንካራ መሆን ይጠበቅብናል አስቀድመን ፈቃደ እግዚአብሔርን እንጠይቅ በምክረ ካህን እንታገዝ እስከ መጨረሻው የሚፀና እርሱ ይድናል ነው የሚለው አሁን ደግሞ የፈተና ሰዓት ነው ምንም ይሁን ምን ደግሞ ይሁን ክፉ እግዚአብሔር ፈተንኝ እንዳትል እግዚአብሔር በክፉ አይፈትንምና
ዮሐንስ፦ ክፋውን ምን አመጣው ብርቄ እኔ እኮ የድንግል ልጅ ነኝ አለማፍም ክርስቶስ ነው አውነቱን ልንገርሽ አንቺ ለእኔ ስታስቢልኝ ነው ካንች ጋር መኖርን ያሰብኩት አንድ ትልቅ አባት ባለፈው ቤተ- ክርስትያን ስንገናኝ ስራ መስራት እንደ ምፈልግ ስነግራቸው ደስ አላቸውና በርታ አሉኝ ዛሬ ጠዋት ኪዳን ሲያልቅ ስራ አገኝህ ወይ አሉኝ አለማግኘቴን ስነግራቸው ምን እንዳሉ ታውቂያለሽ
ብርቄ፦ ምን አሉህ?
ዮሐንስ፦ በወር ሰባት መቶ ብር ልክፈልህና ድርጅቴ ውስጥ መኪና ያዝ አሉኝ
ብርቄ፦ ምን! ምን አልካቸው?
ዮሐንስ፦ እንቢ ነዋ!
ብርቄ፦ ለምን ዮሐንስ?
ዮሐንስ፦ ሰውዬው ተረድተውኛል ስራን በፈለክ ጊዜ ጀምር ነው ያሉኝ አሁን አልችልም የጌታን ያም እኔም ገዳም ሆኜ ሱባኤ መያዝ እፈልጋለው
ብርቄ፦ እግዚአብሔር ይባርካቸው እመቤቴ ትጠብቃቸው
ዮሐንስ፦ ይኸውልሽ ብርቄ ለፋሲካ ነው እዚህ የምገባው ምን አልባትም ከማድቃኔ ስመለስ ለአባዬ አንድ ላይ ለመኖር መወሰናችንን እንነግረዋለን አስከዚያው ግን አንቺም ጸሎት አድርጊ የስራውን ጉዳይ ልነግርሽ ነው የመጠሁት አሁን ቅዳሴ ሰዓት ስለደረሰብኝ ጫማ ልቀይርና ልሒድ ይሒን እንኪ /የእመቤታችንን ስዕ-ስዕል ይሰጣታል ተቀብላ ተሰቅለዋለች አቶ ጌታቸው ይገባሉ/
አቶ ጌታቸው፦ ብቻሽ ነሽ እንዴ ብርቄ?
ብርቄ፦ አይ ዮሐንስ አለ
አቶ ጌታቸው፦ አንድ ላይ ናችሁ እ....እ ጥሩ በጀ ብያለው
ዮሐንስ፦ ሰላም ዋይ ብርቄ ..... ውይ አባዬ መተሃል እንዴ
አቶ ጌታቸው፦ ሰሞኑን ምነው አልታይ አልከህ ጸባይህ ሁሉ ተለወጠብኝ
ዮሐንስ፦ ኧረ አልተለወጠም አባዬ በጣም አረፍዶብኛል አዚህ ቤት እንደ ባዕድ አየታየው መሆኔን ግን ቸል አትበለው /ይሒዳል/
አቶ ጌታቸው፦ ምን ሆኖ ነው እንደዚህ የሚለኝ አንቺ
ብርቄ፦ እኔኛ አባዬ
አቶ ጌታቸው፦ እንዴት እኔንኛ ከእኔ ጋር ሲጫወት ቢውል ቢያድር የማይጠግበው ልጅ ዛሬ እዚህ ቤት እንደ ባዕድ አየታየው ነው ይላል የሆነ ነገርማ ይኖራል ምንም የነገረሽ ነገር የለም?
ብርቄ፦ ኧረ የለም
አቶ ጌታቸው፦ የተናገረው ሰው አለ?
ብርቄ፦ ኧረ የለም ገና አሁን መምጣቱ ነው
አቶ ጌታቸው፦ እና ገና መግባቱ ከሆነ ምን እንደዚህ ያጣድፈዋል የቤቱ በዕድ ነኝ የሚለውስ ምንድ ነው?
ብርቄ፦ አይ .....አባ.... ግን አባዬ..... ዮሐንስ .....
አቶ ጌታቸው፦ ዛሬ እዚህ ቤት ምን ሆናችኋል አትናገሪም እንዴ?
ብርቄ፦ ምንም የመናገር መብት የለኝም እዚህ ቤት ውስጥ ግን ትልቅ ማዕበል እንደተነሳ ይገባኛል አባዬ..... እመቤት.....
አቶ ጌታቸው፦ ምን ሆነች እመቤት?
ብርቄ፦ ለዚህ ቤት ያላት አመለካከት ጥሩ አይደለም
አቶ ጌታቸው፦ ምን አልሽ?
ዳዊት፦ አንቺ ጥጋብሽ አፍንጫሽ ላይ ደረ አይደል ላንቺ ክብርና ቦታን ስለሰጠንሽ .....
አቶ ጌታቸው፦ ምንድነው ዳዊት?
እመቤት፦ ምንም አይደል ዳዊት ተወው በቃ
ዳዊት፦ እንዴት እተወዋለው በቤቴ ስገፋ ስሰደብ ስደበደብ ይሒንንማ ዝም አልልም ማነው ግን አይዞሽ ያለሽ እንዴት ብትደፍሪ ነው የምትሰድቢያት?
አቶ ጌታቸው፦ ማነው ተሳዳቢው?
ዳዊት፦ ያንተው ቀበጥ ሰራተኛ ነቻ
አቶ ጌታቸው፦ ብርቄ እኮ ማንን?
ዳዊት፦ አታያትም እሙን ..... ተመልከታት እንዲህ አሰክትሆን ድረስ
አቶ ጌታቸው፦ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ብርቄ፦ አይደለም
እመቤት፦ ተመልከት አባዬ በዱካ እኮ ነው የመታችኝ
አቶ ጌታቸው፦ እንዴት አንቺ
እመቤት፦ ተወው አባዬ ትንሽ ነገር ነች
አቶ ጌታቸው፦ እንዴት ትንሽ ከዚህ በላይ አስከምትገፀሽ ድረስ ነው የምጠብቀው
ዳዊት፦ እኔም የማይገባኝ ይህ ነው እዚህ ቤት ግን ለዚች ሰራተኛ እንደልቧ እንድትፈነጭ ማነው ያደረጋት?
ብርቄ፦ ኧረ ባክችሁ
አቶ ጌታቸው፦ ምን ቀረሽ ብርቄ .... አሃ ቅድም መዕበል ስትፅኝ የነበረው እራስሽ አዘጋጅተሽልኝ ኖሯል ..... ምን አይነት ወባይ ነው ያለሽ እስከ ትላንት የቤቱ አሳቢ አዛኝ ተቆርቋሪ ነበርሽ ዛሬ ምን ተገኘ?
ብርቄ፦ ለምን እድል እንደማትሰጡኝ አይገባኝም
እመቤት፦ አይ ችግር የለም እኔ ከዚህ ቤት እወጣለው አንቺና ተቆርቋሪሽ ዮሐንስ ግን እዚህ ኑሩ
አቶ ጌታቸው፦ ዮሐንስ ..... ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው እርሱ ነው አይደል
እመቤት፦ ዳዊት በቃ እኛ ከዚህ ቤት ወጥተን ተከራይተን እንኑር የእሷ ሃሳብ መጨረሻ ልጅን ዮሐንስን አግብታ ለመኖር ነው
አቶ ጌታቸው፦ ጥሩ ስትማከሩ ኖሯል ..... ሞቼ ነው ቆሜ ልጄን ለሰራተኛ የምሰጠው
እመቤት፦ ተሳት በቃ በእኔ ምክንያት አትቅጧት እኔ ፀቅር ብያታለው
ዳዊት፦ አየሽ አይደል ..... እንዲህ ተበድላ ላንቺ ተቆረቆራለች ነገሩ አንቺ ምን አደረግሽ ያጠገበሽ ያ የገዛ ወንድሜ ለካ የእሱ ሃሳብ እኛን አስወጥቶ ካንቺ ጋር መኖር ነው
ብርቄ፦ በቃችሁ ከዚህ በላይ አልችልም የምትፈልጉት ከዚህ ቤት እንድወጣ ነው አይደል ጥሩ /ወደ ውስጥ ትገባለች/
አቶ ጌታቸው፦ ይችን ይወዳል ጥጋብ
ዳዊት፦ ስህተትህን አየኸው አይደል አባዬ ያንተ ማቅበጥ ያንተ እንደ ቤተሰብ ማየት ያመዋውን ጣጣ የእሷ አይገርመኝም የሚገርመኝ ደግሞ የዮሐንስ ከእሷ ጋር ማሽቃበጥ እሷ ብታስብ የዚህን ቤት ሃብት ለመውረስ ነው እሱ ግን ቆይ ምን አይቶባት ነው?
እመቤት፦ እሱ እኮ ምንም አያውቅም የሆነ ነገር አርጋበት ቢሆንስ?
አቶ ጌታቸው፦ ምን ማደረግ እንዳለብኝ እኔ አውቃለው /ወደ ውስጥ ይገባሉ/
ዳዊት፦ እኔም የማደርገውን አውቃለው ወይ እኛን ወይ እሷን ይመርጣል /ወደ መኝታ ቤቱ ይገባል/
እመቤት፦ /በመንፈስ ስትጨነቅና ስትጮኽ ትታያለች/
ብርቄ፦ /እያማታበች ትገባለች/
እመቤት፦ እስከ አሁን አቃሽን አስረሽ አልጨረሽም እንዴ? ቆይ አንቺ ግን ምን አይነት ቋንቋ ነው የሚገባሽ?
ብርቄ፦ አረብኛ ..... ታውቂያለሽ ከዚህ ወደ ውስጥ ስገባ ከዚህ ቤት የነበረኝን ዝምድና ሁሉ ሰብሬ ለመምጣት ነበር አሁን ግን አዚህ መኖር ነው የምፈልገው
እመቤት፦ ፓራሳይት ሆኗ ውስጥ ተጣብቆ መኖር አያሰለችሽም
ብርቄ፦ ጠዋት ለአባዬ የሰጠሽውን ወተት ውጪ ደፍቼው ነበር ድምቷ ወተቱን ልላው ሞታ አገኘዋት እ..... እ.... አሁን ከእዚህ ቤት መውጣት እንደሌለብኝ አመንኩ አባዬ ውጪ ብሎ አስካላሰወጣኝ አልወጣም።
እመቤት፦ ምን አይነት ደረቅ ነሽ
ብርቄ፦ አሁን አሁንማ ሳስበው የዮሐንስ የምግብ መበከል መንስኤው አንቺ ነሽ መሰለኝ ከእንግዲህ እኔም አልወጣም አያዋና ድመት ሆነን እንኖራታለን
እመቤት፦ አልወጣም! /ብርቄ ወደ ውስጥ ልትገባ ስትል/ እናያታለና ምን አይነት ጉድጓድ እንደ ምምስልሽ አሳይሻለው
ብርቄ፦ ጉድጓዱን አታሪቂው እ ..... መታመን እንደሚከብደኝ አምናለው የእኔ መድሃኒአለም ግን አንድ ነገር ያሳየኛል /ትገባለች/
እመቤት፦ /ብቻዋን እያሰበች ትንጎራደዳለች/
አቶ ጌታቸው፦ እመቤት ንገሪኝ ምን እንዳለችሽ
እመቤት፦ ተወው አልኩ እኮ አባ
አቶ ጌታቸው፦ እውነት አንቺ የምትወጅኝ ከሆነ ስራዋን ንገሪኝ
እመቤት፦ አባዬ ስራዋማ ብዙ ነው የእኔ መሰደብና መመታት አያገርምም ዮሐንስና እሷ ምን ሲሉ እንደሰማውታውቃለህ አባዬ አባትህ አይደለም በህግንነትህ ተዋለህ ስለተገኘህ አሳድጎህ ነው ስትለው ሰማዋት
አቶ ጌታቸው፦ እኮ ታዲያ ..... ለዚህ ነዋ ደረቱን የነፋብኝ በሳደኩኝ ባበላው በጎረስኩ ኧረ ለመሆኑ ምኗን ተማምኖ ነው ለአይኑ ያስጠላሀት?
እመቤት፦ /ውሃ ቀድታ ትሰጣቸዋለች/
አቶ ጌታቸው፦ /ሲጠጡ ያማቸኋል ልባቸውን ይይዛሉ/
እመቤት፦ ይሒ ብቻ መሰለህ አባዬ እዚህ ቤት ወንድ እንደሚያድር ታውቃለህ?

አቶ ጌታቸው፡- የምን ወንድ ከውጪ?
እመቤት፡- አዎ ከውጪ እኔ እኮ የምታውቅ ነው የሚመስለኝ
አቶ ጌታቸው፡- ለምን እስከዛሬ አልነገርሽኝም?
እመቤት፡- ሶስና የነገረችህ መስሎኝ
አቶ ጌታቸው፡- ሶስና!
እመቤት፡- አታውቅም እንደ አባዬ ሶስና እኮ አርግዛለች?
አቶ ጌታቸው፡- /ልባቸውን ይዘው ይወድቃሉ ታነሳቸዋለች ወደ ጓዳ ሲገቡ ተከትላ ሔዳ ትገፈትራቸዋለች/
እመቤት፡- ኡ....ኡ....ኡ...ኡ ዋይ
ዳዊት፡- ምንድ ነው ምንድነው እሙ?
እመቤት፡- ብርቁ አባትህን ገፍትራ ገደለቻቸው

መብራት ይጠፋል

/አቶ ጌታቸው ዊልቸር ላይ ተቀምጠው ይታያሉ እመቤት ወትት ይዛ መዋታ ትሰጣቸዋለች ብርቁ ወተቱን ተቀብለቸው ወደ ውስጥ ትገባና መድኃኒትና ሰዋታቸው ተመልሳ ትሔዳለች/
አቶ ጌታቸው፡- ጌታ ሆይ ምነው እረሳኸኝ አይዋቼ በሃዘን ተሞልተዋልና ባሪያህን እኔን አሰናብተኝ ልጆቼም በእኔ ላይ ተነስተውብኛልና የእኔ የኃጢአተኛውን ጸሎት ሰማ ምነው አመብርሃን አውን ኃጢአቴ በገዙ ነው ያልሰማሽኝ እባክሽኝ በልጆቼ ጭካኔ አትቅጭኝ እባክሽ የምህረት እጅሽን ዘርጊልኝ እኔ ባሪያሽ በጠላት ዲያቢሎስ ተከብቤአለውና እባክሽ እጅሽን ዘርጊልኝ እናቴ እመቤቴ አፌን የፈታውብሽ ቋንቋዬ ያላንቺ ማን አለኝ ለእኔ እባክሽ ፍቅርን አሳድረልን እኔ እኮ አቅም የለኝም እናቴ ደጅ እንኳን እንዳልጠና ምርኩዝ የለኝም እናቴ እባክሽ ጸሎቴን ከደመና በታች እንዳያቀር ከልጅሽ ከወዳጅሽ አማልጅኝ እርሱ ቸር መሃሪ ይቅር ባይ ነውና /ምርር ያለ ለቅሶ እና ፀዋታ/
እመቤት፡- ምነው ተከዝክ አ....ባ....ዬ አ...አ... አ አባዬ.....
አቶ ጌታቸው፡- የእግዚአብሔርን ተሰፋ እየጠበኩ
እመቤት፡- እግዚአብሔር ..... እግዚአብሔር ....እግዚአብሔር ያንተ እግዚአብሔር የታለ ለምን አይታይም ..... መቼ ነው የሚፈርድልህ የእኔን አምላክ ተመልከት ቁጭ ብሎ ቡናውን እየጠጣ ይፈርዳል ለልጆቹ ስኬትን ይሰጣል እውነት ስግደት ሁሉ ለእንተ ለአባ ጠቋር ምስጋና ሁሉ ለእንተ ለአባ ጠቋር ጀበና፣ ሲኒው፣ ቡናው፣ አተላው፣ ሽቶው፣ በጉ፣ ቀንዱ ኧረ ሁሉ ለእሱ ...ከአባ ጠቋር ....አ...እ..እ አየህ አይደል የእኔን አምላክ እንባዬ ፈሶ አልቀረም ተበቀለልኝ ያንተ አምላክ የታለ የታለ የአንተ አምላክ?
አቶ ጌታቸው፡- ይመጣል ይመጣል የእኔ አባት እጁን ከአርያም ይልካል እርሱ ሲናገር የሚያቆመው የለም አጋንት ሁሉ በፊቱ ይንቀጠቀጣሉ ጉልበት ሁሉ ለእርሱ ይሰግዳል አባባ ጠቋር ቡና ጀበና እንደ ትቢያ ይረግፋል
እመቤት፡- አ...እ..አ ባይመጣስ ባይፈርድስ?
አቶ ጌታቸው፡- እርሱ የታመነ አምላክ ነው ባይመጣም ባይፈርድም በእርሱ ዘንድ የተሻለ ነገር አለ ያንን አብዝቼ እጠይቀዋለው ስለ እኔ ኃጢአት ሳይሆን ስለ እናቴ ልመና ስለ ድንግል ማርያም ጸሎት ሲል ይሰማኛል
እመቤት፡- ምን አይነት ጸሎት ..... የት.....እዚህ ..... አ....አ...አ... አላየኸውም እንዴ ልጅህ ዋሎ ሲሄድ አ.....አ...አ... ስማኝ አባዬ አያንዳንዷን እንባዬን አቆጥራለው ያሳደከው ልጅህ ከሀሰቲቃል ባትወጣ ለምን ጭሎህ ሔደ ለእንተ ጸሎት ሊያደርግ ይሔማ የብርቁ ወሬ ነው አውነቷ ግን እኔ ነኝ ማን ዘራሽነቱን ነግሬ ያላስተማርከውን ምክንያት ነግሬ በልቡ ጥላቻን ሞልቼ አሸፈትኩት ምን አልባት አንድ ቀን አሱም አውሬ ካልበላው አብደቱ ሲለቀው ይመጣል
አቶ ጌታቸው፡- ዮሐንስ እንደዚህ አያደርግም
እመቤት፡- ምን ዮሐንስ ብቻ ሶስና ብትሆን
አቶ ጌታቸ፡- ሶስና እሷን ደግሞ ምን አረግሻት?
እመቤት፡- ሶ...ስ...ና ምስኪን የጌታ ባሪያ አባቴን ይቅርታ ልጠይቀው ስትለኝ እንኳን ለይቅርታ ለሰላምታ ኧረ ለማየት እንደ ተጠየቄት ነግሪያት የመታመምዎ ምክንያት እርሷ መሆኗን አሳምኜ ለአይን እንደ ጠሏት ነግሬ ለፅንሷ ማስወረጃ ሰረ ምሺ ቅጠል በዋሺ አጠዋቻት ነፍስ ውጪ ነፍስ ግቢ ስትል ቅቾት መጣው ምን ይታወቃል ይሔኔ መዘጋጃ ..... ምን አልባት ብትድን እንኳን ከመድኃኒቱ ኃይለኛነት የተነሳ ማህፀኗ ለዘለአለም ..... እብደት ይሆናል አጣዋ
አቶ ጌታቸው፡- ይሔንንም አሰማኸኝ ጌታዬ ..... ኧረ ባክህ የእኔን ኃጢአት በእኔ ላይ ለምን በልጆቼ /ያለቅሳሉ/
እመቤት፡- አ....አ....አ..... እንባ..... እንባ አባዬ የታል የለም እግዚአብሔር
አቶ ጌታቸው፡- በዳዊት አንደበት ይናገራል ልጂ ዳዊት ሲመጣ ሁሉንም ነገር ዘርዝሬ አሳገረዋለው እሱ እኔን ይሰማኛል
እመቤት፡- ዳዊት ማነው ዳዊት .... አሃ ያ የእኔ ባሪያ ለአባቴ ቡና የሚያፈላው ከእኔ ጋር ለአባ ጠቋር የሚሰግደው እሱማ ከእግሬ በታች ነው ውይ አባዬ አርብ አርብ ከሠአት እኮ እግር አዋቦ የመጀመሪያውን የእግር አጣቢ የሚጠጣው ከዚያም የሚያጠጣው.....
አቶ ጌታቸው፡- በቃሽ! ..... የኔ ልጅ በፍፁም ይሔንን አያደርግም
እመቤት፡- የአባት ስም አይቀየርም እንጂ ስሞን አርሱ በአባ ጠቋር ይለውጠው ነበር

አቶ ጌታቸው፡- እንኳ መሰሪ /ከዋልቸራቸው ላይ ተነስተው ሊያንቋት ሲሉ ይወድቃሉ/
ዳዊት፡- /ከውጪ ይ/ ት...ዕ...ይ...ን...ት (ያ) /አ...ራ...ት.../
እመቤት፡- ብረቁ ኧረ (ሳቁ) ነው
ዳዊት፡- እንዴ ምንድነው እሱ?
እመቤት፡- አርዳኝ እባክህ አግዘኝ ዳዊት /አንስተው ዊልቸሩ ላይ ያስቀምጧቸዋል/
ዳዊት፡- ምንድነው እመቤት ምንድነው እሱ?
እመቤት፡- አታይም እንዴ ተአምር
ዳዊት፡- የምን ተአምር?
እመቤት፡- ከመቀመጫቸው ተነስተው እኮ ነው አዚህ የደረሱት
ዳዊት፡- እንዴት?
እመቤት፡- በላያቸው ላይ የሰይጣን መንፈስ ነበረ አንዴ ሰው አንዴ አፈር ያደርጋቸኋል
ዳዊት፡- የምትሒው አልገባኝም?
እመቤት፡- በመጀመሪያ ልጂ አንቺ ባትሚረ ሰው አልሆንም አወድሻለው አሉኝ መለስ አሉና ማነሽ አንቺ ምን ትሰሪያለሽ ብለው ማንጓራት ጀመሩ እንደገና ሌላ ወሬ መንፈሳቸው ከለፈለፈ በኋላ ወደ ማንነታቸው ሲመለሱ እጂን ዘረጋሁላቸው ቀስ እያሉ ወደ እኔ ተጠጉ በመሃል መንፈሳቸው ተነሳና ወደቁ
ዳዊት፡- ምን እናድርግ ታዲያ ድኝ ምናምን እናጭስ አንዴ መንፈስ ከሆነ?
እመቤት፡- እንደ እኔ እንደ እኔ አባታችን ጋር ብንወስዳቸው ሳይሻል አይቀርም
ዳዊት፡- አባዬ እሺ አይልም
እመቤት፡- ምን ነክህ ዳዊት አስረናቸውም ቢሆን ይዘናቸው እንሂዳ
ዳዊት፡- አባዬን አሰረን?
እመቤት፡- ለአሳቸው ደህት እኮ ነው ዳዊት በዚያ ላይ ይፈወሳሉ
ዳዊት፡- አይ እንደዚህ እንኳን አይሆንም ለማንኛውም መጣው
እመቤት፡- /አየተንገዳደደች ታስባለች/
አቶ ጌታቸው፡- /እንደመንቃት እንደ መባነን ብለው/ አባክሽ ልጂ ይቅር በይኝ .....
እመቤት፡- ዳዊት ...ዳዊት ናና ቶሎ በል
አቶ ጌታቸው፡- እባክሽ ልጂ ይቅር በይኝ ..... እመቤቴ ኧረ ባክሽ...
እመቤት፡- ስማው መንፈሱን ሲያስጨንቃቸው
አቶ ጌታቸው፡- /ጮክ ብለው እንደመንቃት እያሉ/ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ዳዊት፡- አባዬ
እመቤት፡- ቆይ ቆይ ቆይ አንተ አትታያቸው
ዳዊት፡- ይደበቃል
እመቤት፡- ሶስና አባዬ
አቶ ጌታቸው፡- ልጂ ይቅር በይኝ .....ዞር በይልኝ ዞር በይልኝ አንቺ
እመቤት፡- ዳዊት ...ዳዊት
ዳዊት፡- ምነው አባዬ
አቶ ጌታቸው፡- እንኳን መጣህ ልጂ ..... ዳዊት የእኔ ልጅ አንተ ብቻ ነህ የቀራኒኝ አንተ እንኳን ተራዳኝ ይቺ ልጅ ልጆቼን ጨርሳለች አንተንም ትገልሃለች
ዳዊት፡- ወይኔ ጉደ አባባ ምን ሆነክ ነው
አቶ ጌታቸው፡- ስማኝ የአኔ ልጅ የምንግርህን
እመቤት፡- አይዘህ አባዬ ምንም አትሆንም
አቶ ጌታቸው፡- አትንኪኝ አንቺ የሠይጣን ቁራጭ ቤተሰቤን ልትጨርሺ ነው እንዴ .... ዳዊት
ዳዊት፡- ቆይ አባባ ተረጋጋ ..... መንፈሱ ነው አይደል እንደዚህ የሚያደርገው
እመቤት፡- አልኩህ እኮ ቅድም ልጂ እመቤት አሁን አይንሽን ላፈር መንፈሱ እኮ ነው እንደዚህ የሚያደርገው
አቶ ጌታቸው፡- መንፈስ የለብኝም አንተ አርኩስ መንፈስስ የአንተ ሚስት
ዳዊት፡- አባዬ
አቶ ጌታቸው፡- እራሴን የማላውቅ አይምሰልህ አውቃለው ብታመም ጸበል እንጂ ጠንቋይ አልሻም ይችህ እርጉም ሚስትህ ግን አሳበደችኝ ልጆቼን ዮሐንስንና ሶሲናዬን አሳጣችኝ
ዳዊት፡- አባዬ እርጉም ነው ያልከው
አቶ ጌታቸው፡- አዎ ልጂ
ዳዊት፡- እስከ ትላንት ላንተ ጥሩ ነበረች አይደል ታዲያ ዛሬ ምን ተገኘ
አቶ ጌታቸው፡- አንተም ዳዊት አንተም በዚች ከይሲ
ዳዊት፡- በቃህ አባዬ ካሁን በኋላ ሚስቴ ስትዋሪድ ማየት አልፈልግም
አቶ ጌታቸው፡- አባትህስ ዳዊት ..... የእኔን እውነት ላለመስማት መረረህ አባክህ አንድ ጊዜ ስማኝ
እመቤት፡- አባክህን ስማቸው ዳዊት
ዳዊት፡- አልችልም እንደ ከዚህ በፊቱ ይቅርታ ብለሽ ስትወድቂ ማየት አልችልም

አቶ ጌታቸው፡- ጎበዝ የእኔ ልጅ አሁን ኮራውብህ አንተ የሚስትህን ጉድፍ ለመሸፈን የአባትህን አንድ ቃል አትሰማም ጎበዝ በርታ ልጄ ከልጅነትህ ጀምሮ ስሰማህ የኖርኩኝ ዛሬ ለትንሽ ደቂቃ ጆሮህን ስጠኝ ስልህ እንቢታ ነው መልስህ ዋሩ ዋሩ ነዋ ብርቄ .....ብርቄ .... ብርቄ አንዴ ላስቸግርሽ ብርቄን ትጠሪልኝ
እመቤት፡- ብርቄ ....አንቺ ብርቄ ጆሮሽ ተደፍኗል እንዴ
አቶ ጌታቸው፡- በቅርብ የሚረዳኝ እንዳይኖር ከዚህ ቤት አራቃችኋት ማን ሰሚ አለኝ
ብርቄ፡- አቤት
አቶ ጌታቸው፡- ወደ ከፍሌ አስገቢኝ /እየገፋች ታስገባቸዋለች/
እመቤት፡- ቶሎ በፍጥነት ነፃ አሁን እፈልግሻለው
ዳዊት፡- ብርቄ ቤት ቀየረች እንዴ?
እመቤት፡- ተራቅትን እኮ ዳዊት አንድ ዕቃ አስቀምጬ አላገኘውም ብር በየጊዜው ነው የሚጠፋብኝ ታዲያ ምን ላድርግ ዳዊት?
ዳዊት፡- በአሉ ይለፍና አሰናብታታለው እስከዚያ ሌላ ሰራተኛ እንፈልጋለን
እመቤት፡- ጠዋት ጊዝ ያልከኝን መድኃኒት እኮ ሳልገዛ ቀራው
ዳዊት፡- ትቼቄን አሁን ሰዎት
እመቤት፡- ብር ጠለሌለን እኮ ነው
ዳዊት፡- ቀፀ አሰጥሻለው .....አ.... እሙ....ነገ አባዬን አባታችን ጋር እንወስደዋለን
ብርቄ፡- አባታችን ጠንቋይ ቤት በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ዳዊት፡- አንቺን አይመለከትሽም ..... እንደውም ዋሪው ይዘሽው ነፃ ተነጋግረን ይተኛታል
እመቤት፡- የመድኃኒት ሰዓቱም አልፏል ዋሪው
ዳዊት፡- የዚች ልጅ ጥጋብ የቤቱን ጣሪያ ነክቷል
እመቤት፡- ምን ይደረግ የወጡን አናት የምትበላው እሷ
አቶ ጌታቸው፡- ጆሮህን ልትሰጠኝ ነው?
ዳዊት፡- በመጀመሪያ መድኃኒትህን ውሰድ
ብርቄ፡- መድኃኒት አልቆ አይደል እንዴ ጠዋት ያልዋጠው?
እመቤት፡- ሁለት ደብቄ አስቀምጬለት ነበር
ብርቄ፡- ለምን?
እመቤት፡- ሲብስበት ልሰጠው
ብርቄ፡- አልባሰበትም ይቅርበት
ዳዊት፡- አፍሽን አትክፈቺ ..... ሰራተኛ እኮ ነሽ
አቶ ጌታቸው፡- ያውም ታታሪ ..... ምነው ዳዊት ሠራተኛ አይደለህ ሚስትህም ብርቄም ታዲያ ምን ለየው?
ዳዊት፡- መድኃኒትህን ውሰድና እንነጋገራለን
ብርቄ፡- ቀፀ ውሃ ላምጣ
እመቤት፡- /ውሃው ውስጥ መድሃኒት ጨምራ ታመጣለች/
ብርቄ፡- ይሔን ነው የሚጠጣው
ዳዊት፡- ለምን ለምን አንቺ?
ብርቄ፡- ይሔማ መርዝ ነው
ዳዊት፡- መርዝስ ከአፍሽ የሚወጣው /ከእመቤት ተቀብሎ ሊያጠጣቸው ሲል ተቀብላ ትጠጣዋለች ያመጣችሁንም ለአቶ ጌታቸው ትሰጣቸዋለች/
ዳዊት፡- አየሃት አይደል አባዬ?
አቶ ንጉሴ፡- የሚስትህ ቢሆን ንክች አላደርጋትም ነበር
ዳዊት፡- ዋሩ ነገ አርብ ነው አባታችን ጋር እንሔዳለን
አቶ ጌታቸው፡- ሌላ አባት ኖሮሃል እንዴ?
እመቤት፡- አዋቂ ጋር ለማለት ነው
አቶ ጌታቸው፡- እውቀቱን ይንሳችሁ የእራሴ እውቀት እያለ ሌላ አዋቂ አልፈልግም
ብርቄ፡- አዎ ጠንቋይ ቤት አይሔም
ዳዊት፡- ምን አባሽ አገባሽ?
አቶ ጌታቸው፡- ጠንቋይ ..... አ...አ... አልሞትኩም እኮ አንተ አራሳዬም ጠንቋይ ቤት አይሔድም
ዳዊት፡- ላንተ አስበን እኮ ነው አባዬ
አቶ ጌታቸው፡- ለራስህ አስብ ለካ እየሄድክ ታፈነድድልኛለህ ነገሩ ሁሉ እውነት ነዋ ስማኝ በሰህተት ይህንን ቃል ብሰማ ልጄ መሆንህን አስከመጨሻው አረሳዋለው
ዳዊት፡- ምንድ ነው አለማህ እንደዚህ ሆነህ ለመኖር ጡረታ ሚንስቴር አይደለውም እኮ
ብርቄ፡- ይሔን ያህል ከፉ ቀን አልመጣም ምነክህ ዳዊት?
ዳዊት፡- ዝም በይ አንቺ ወፈኛ ይህ ሁሉ ያንቺ ጣጣ ነው የጠጣሽው መርዝ ነው ስትይ አለነበር እሺ አሁን ምን ሆንሽ? ወራኛ
አቶ ጌታቸው፡- ሽከም ሆንኩብህ .....አይዞህ አትፍራ ያንተ እራፊ ፈላጊ አይደለውም እግዚአብሔር የሰጠኝ ቤት አለ ሽጬውም መኖር እችላለው
እመቤት፡- ሽጪ! እንዴት ይሸጣል?
ዳዊት፡- የአናቴ ቤት ነው ቤቱማ አይሸጥም
ብርቄ፡- ኧረ ስለፈጠራችሁ ጋሼ ምን ነክህ?
ዳዊት፡- ሒጂ መድኃኒቱን ገስተሽ ነፃ /ልትወጣ ስትል/
ብርቄ፡- /ራሷን ይዛ/ ወይኔ በስመ አብ....
አቶ ጌታቸው፡- ምን ሆነሻል ብርቄ?
ብርቄ፡- አይ....ምንም /ወጥታ ትሔዳለች/
እመቤት፡- /ስልክ ታነሳለች/
ዳዊት፡- ምነው?
እመቤት፡- አይ ምንም ምልክት ማድረግ ፈልጌ ነው
አቶ ጌታቸው፡- ምነው አንተ የእስራኤል አምላክ ከቤቴ አስከራቾት ድረስ
ዳዊት፡- ቤቴ ቤቴ አትበል የዚህ ቤት አስተዳዳሪ እኔ ነኝ የአናቴ ወራሽም እኔ ከፈለክ ፍርድ ቤት ልትከሰኝ ትችላለህ
እመቤት፡- አይዞህ አባባ አሁን ሁሉም እኮ ካዶት
አቶ ጌታቸው፡- ለእኔ አንድ ብርቄ ትበቃኛለች
እመቤት፡- አ..... አ....አ... ብርቄ አ...አ...አ.... ዋሩ ነገር ተዘጋጅቶላታል ትመለሳለች ብለህ እንዳታስብ እኔ የገዛዋቸው ጎረምሶች ሥጋዋን ለሰሚያ አሞራ ደሟን ለምድር አራዊት .....
አቶ ጌታቸው፡- /ከሚልቸራቸው አይደቂ በኃይለኛ ጩኸት/ ብ...ር...ቄ!

.....ትዕይንት አምስት ይቀጥላል ....././/

-

/አቶ ጌታቸው አቤት ቁጭ ብለው ጥቁር በጥቁር ለብሰው ዳዊትና እመቤት አንዴ ወደ ጓዳ አንዴ ወደ ሳሎን እያሉ ሻንጣ ሲያስተካክሉ ይታያሉ/
ዳዊት፡- አባባ ከእኛ ጋር ብትሔድ ደስ ይለን ነበር
አቶ ጌታቸው፡- የት ጠንቋይ ቤት?
ዳዊት፡- ጀመረህ ደግሞ አንዳንዴም ለእኛም አስብልን እንጂ በአንተ የተነሳ ስንት ነገር አየን እመቤትም ስራ አቆመች ዛሬ እንኳን ተረዳት ይሔው ከበአሉ ዋዜማ ከትላንት ጀምሮ እንቅልፍ የለትም ለማን ስትል ይመስልሃል?
አቶ ጌታቸው፡- እሺ አሁንማ የፈቃዳችሁ ተገዢ ነኝ እንደፈቃዳችሁ
እመቤት፡- የቀራኝ ይሔ ብቻ ነው ግባና ልብስህን ቀይር
ዳዊት፡- ዛሬ የአንቺን ምርጫ ነው የምለብሰው
እመቤት፡- እሺ ቶሎ በል /ተያይዘው ይገባሉ/
አቶ ጌታቸው፡- ይሁና .... አይ ልጄ እነዚህ አስር ቀናቶች እንዴት እንዳለፉ እኔና እግዚአብሔር ነን የምናውቀው የሰው ልጅ የፈለገውን በደል ቢበድል የሞት ፍርድ የሚያስፈርድ በደል እንኳን ቢሰራ በምግም አይቀጣም አንቺ ብርቄ ነፍስሽን ይማረዋ እውነት እኔ እንዳልራብ እንደተንከባከብሽኝ መልስክት የሰይወትን ምግብ ይመግቡሽ እንዳልጠማ እንዳጠጣሽኝ ቅዱሳን ከሕይወት ውሃ ምንጭ ያጠጡሽ ሌላ ምን አላለው ደሀና .....ይሁን ..... ይሁና እግዚአብሔር ያንተ ፈቃድ ይሁን
እመቤት፡- ዛሬ ትንሳኤ አይደለም አባዬ?
አቶ ጌታቸው፡- የጌታ እንጂ የጠንቋይ ትንሳኤ የለውም
እመቤት፡- በትንሳኤው ማነው ደስተኛ እኔ ወይስ አንተ?
አቶ ጌታቸው፡- በትንሳኤማ ደስታው ለአዳም ልጆች ሁሉ ነበር የሚገርመኝም ይሔ ነው
እመቤት፡- ምኑ ነው የሚገርመው?
አቶ ጌታቸው፡- የእኛ አምላክ አያዳላም ዶሮ ወጥ አምጡልኝ አይልም ኃጢአተኛ ነው ባድቅ ነው ብሎ አይለይም እናንተ ሽከማችሁ የከበደባችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለው ነው የሚለው
እመቤት፡- እና እኔ የሰጠውህን ሽከም እሱ ይሸከምልሃል ማለት ነው?
አቶ ጌታቸው፡- እንደ እኔማ ቢሆን መች እችለው ነበር
እመቤት፡- አይሳሳቱ እንጂ ትልቅ አዋቂ አይደሉም እንዴ?
አቶ ጌታቸው፡- የእኔ እውቀት እኮ ካንቺ ዶክተርነት አይበልጥም አይደል?
እመቤት፡- እንደት?
አቶ ጌታቸው፡- መቼም ዶክተር ለመሆን ትልቅ እውቀት ይጠይቃል በልጄ አይቼዋለው ለራሱ አላወቅ አለኝ እንጂ
እመቤት፡- የእርስዎ ዘሮች ሁሉም ሞኞች ናቸው እርስዎም እንደልጆት ኖት አዎ በእርግጥ ዶክተር ነኝ ግን በሰው ላይ አይደለም እስፔሻሊስትኔቴ በእንስሳ ላይ እንጂ
አቶ ጌታቸው፡- የሰው እስፔሻሊስትማ በሰው ላይ አይጨክንም
እመቤት፡- ያውቁ ነበር ማለት ነው?
አቶ ጌታቸው፡- አዋቂስ እግዚአብሔር ብቻ ነው ግን አንድ ቀን ልጄ ጆሮውን የሰጠኝ ለት ያንቺን እውነታና ማንነትሽን እነግረዋለው
እመቤት፡- ጆሮዎቹ በእኔ የፍቅር ቃል አብደዋል የእርስዎን ወሬ መስማት አይችሉም ተሰፋ አደርጋለው ፀቅር እንደሚሉኝ በነገራችኝ ላይ ትንሽ መሸት አርገን ነው የምንመጣው የሚያስፈልግህን ነገር ማዕድ ቤት አስቀምጬልሃለው ሲርብህም ብላ እናን መጠበቅ ካልቻልክ ተኝተህ ጡብቀን የውጪ ቁልፍ ስላለን ከፍተን እንገባለን
አቶ ጌታቸው፡- ይሔን ሁሉ ለምን ታስቢያለሽ

እመቤት፡- ዳዊት ካንተ መራቅ እንዳለምድ ገባህ /ወደ ውስጥ ትገባለች/

አቶ ጌታቸው፡- ምነው ጌታዬ ሆይ የትኛውን የኃጢአት ስራዬን እንተበቀልከኝ ነው እጆችህ ለእኔ አይዘረጉም እንደ ሰርቼ እንዳልበላ የአልጋ ቁራኛ አደረከኝ ለምኜም እንዳልበላ እረዳት አሳጣሽን አሁን ከእኔ ምንድነው የምትፈልገው ለአጋንት አምላኪዎች ፍፁም ደስታ ለእንተ ወዳጆች ለቅሶ ለምን ጌታዬ ምነው እመብርሃን ልብሽ በእኔ ጠነከረ ለምን አትሰሙኝም ጌታ ሆይ አንተን አምላክ እናትህን አማላጅ ማድረጌ ስህተት ከሆነ እኔም እኮ ሰው ነኝ የተሻለ ነገር አፈልጋለው አንተ የለህም እንዴ ለእኔስ አትፈርድም አሁን ከእኔ ምንድነው የምትፈልገው ልጆቼን በሽሽትና በሞት ነጠከኝ የሰው አውሬ አፍ ውስጥ ከተትከኝ ለምን ለምን አትገለኝም ከዚህ ሁሉ መከራ ግደለኝ

ዳዊት፡- ፈጠን በይ እንጂ

እመቤት፡- ገና እኮ ነው ሠአቱ

ዳዊት፡- ስምንት ሠአት ሞልቷል በአንድ ሠአት ውስጥ መድረስ አለብን አውላው ከወረደ በኋላ ከደረስን አባታችን ይጠሎናል ....አባዬ በል እንግዲ አባታችን ስለዘዙኝ ትቼህ መሒዴ ነው /ሊወጡ ሲሉ ወደ ኋላ ይመለሳሉ/

ዮሐንስ፡- እንኳን አደረሳችሁ አባዬ ..... /ወደ ውስጥ እየገባ/ አባዬ እጅግ በጣም ነው የናፈከኝ ..... ፊትህን በደንብ እንዳይ ግን መጀመሪያ ይቅርታህን አፈልጋለው እባክህን ይቅር በለኝ ስለ እኔ ዕድቅ አስቤ ሆስፒታል ጥፍህ ሒድኩኝ እባክህ አባ ይቅር በለኝና የተራብኩትን ፊቶችህን ልያቸው ጉንጮችህንም ልሳማቸው ትከሻህ ላይ አረፍ ልበል

አቶ ጌታቸው፡- /እያለቀሰ/ አገኛለው ልጄ በሃዘን ተጎድቻለው እንኳን አንተ የአብራኬ ክፋዮችም ትተውኝ ሒደዋል

ዮሐንስ፡- /ከጉልበታቸው ተነስቶ/ <<የአብራኬ ክፋይ>> ..... ምንድ ነው? የምትለው ባዕድነቴን እየነገርከኝ ነው ልጄ አይደለህም ነው እኮ የምትለኝ?

አቶ ጌታቸው፡- ያስነበለለህ እውነት ይሒ አይደል እንዴ?

ዮሐንስ፡- አባዬ ምን ሆኗል .... ምን አስነክታችሁት ነው ..... አናንተን እኮነው የማናግራችሁ?

ዳዊት፡- የሚናገረው የመረረ እውነት ነውና አጣጥመው

ዮሐንስ፡- ምንድ ነው የምትሉት ምንድነው ነገሩ አባ ?

አቶ ጌታቸው፡- በዕድነትህን አውቀህ አይደል አይኑን ላፈር ያልከኝ ሁሉን ነገር እመቤት ነግራለች

ዮሐንስ፡- እመቤት ምን ብላ ..... ምን ብለሽ ነው የነገርሽ አንቺ?

አቶ ጌታቸው፡- ወባይህ የተለወጠው ከሆስፒታል ሸሽተኸኝ የሒድከው አባትህ አለመሆንን ስታውቅ አይደል እንዴ ..... ስማኝ ልጄ ልቤ በሃዘን ተጎድቷል ለወሰቱም የእለት ምግብን በማጣት ገዚሏል ከዚህ የበለጠውን መሸከም አልችልም

ዮሐንስ፡- እኔም የአንተን ሸክም ማብዛት አልፈልግም ..... ነገሩ ምንም ይሁን ምን አንተ አባቴ ነህ ሆስፒታልም ቢሆን ጥፍህ የሒድኩት ከሰው አይደለም ከእግዚአብሔር ጋር ተማክሬ ነው የፈለከውን በለኝ ግን ልጄ አይደለህም አትበለኝ ከልጅነት ክብር አታሳንሰኝ አባዬ እውነት ልጅህ የአብራክህ ክፋይ ካልሆንኩም ያለፈ ታሪኬን አትንገረኝ ለዘለአለም ያንተ ልጅ ሆኜ መኖር ስለምፈልግ አባክህ አባዬ

አቶ ጌታቸው፡- እውነት መራራ ነች ልጄ የአብራኬ ክፋይ ባትሆንም እኔ ግን ከልጅቼ አሳንሼ አላይህም ነበር

ዮሐንስ፡- ለካ ለዚህ ነው ይቅርታዬን የማትቀበለው ታሪኬን ሳላውቅ በፊት እኮ ትወደኝ ነበር .....ግን እኮ አባዬ ታሪኬን ነግረኸኝም አባቴ መሆንህን ውስጤ ይነግረኛል .....አፌን የፈታሁት ባንተ ስም እኮ ነው አባዬ መሒዴ የጀመርኩት ያንተን ጣት ይዤ እኮ ነው አባዬ የጎረስኩት የበላሁት የጠጣሁት ሁሉ ባንተ እጅ እኮነው አባዬ ዛሬም ያንን ቀን አስታውሳለው ከመስከት በላይ ወድቄ በሞትና በሕይወት መካከል ሳለው ዶክተሮች ተስፋ የለህም ሲሉኝ ሁለት ቀን ሙሉ ምግብ ሳትበላ ስለ እኔ መዳን ትጸልይ እንደነበር አውቃለው ታዲያ ለምን ልጄ አይደለህም ትለኛለህ አውነቱን ልንገርህ አባ የወለዱኝ እናትና አባቴ እንኳን ቢኖሩ እንደ አንተ ፍቅርን እንደማይሰጡኝ እርግጠኛ ነኝ ..... አድለኛ እኮ ነኝ አባ አንተ አባቴ ስለሆንክ እንኳንም እናትና አባቴን አላወዛ ይሀን ፍቅርህን ካንተ ሌላ እኮ ማንም አይሰጠኝም እባክህን አባዬ ስለ በደሌም ስለ ኃጢአቴም ይቅር በለኝ በልጅነቴ የፍቅር እጆችህን እንደሰጠኸኝ የይቅርታ እጅህን ዳግም ዘርጋልኝ

አቶ ጌታቸው፡- ልጄ ዮሐንስ ፍቅርህ ልብ ይገዛል በል አሁን አታልቅስ ማልቀስ ለጠላት ለዲያቢሎስ ዛሬ እኮ ትንሳኤ ነው አኔንም ዳግም እግዚአብሔር ሰርቶኛል የጠላት ወሬ ሰምቼ ነው የእኔ ልጅ ይቅር በለኝ ልጄ በል እንባህን አብስ

ዮሐንስ፡- አባዬ በጣም ነው የምወድህ ዳግም ልጄ አይደለህም አትበለኝ

አቶ ጌታቸው፡- እንኳንም ደሜ አልሆንክ ዮሐንስ ደሜ ብትሆን ኖሮ አንተም እንደ ዳዊት ትጠላኝ ነበር አንተም እንደ ዳዊት ጀሮህን ለመስጠት ትከለክለኝ ነበር

ዮሐንስ፡- <<ለመስጠት>> ..... ለምን ጋሼ በምን ምክንያት አባትህ መሆኑን እረስተህ?

ዳዊት፡- ማንንትህን የሰማህ ይመስለኛል አክብሮትህን አልሻም አሁንም ተቀናቃኝ ለመሆን ነው እንዴ አላማህ?

ዮሐንስ፡- ይሒማ ንግግር ያንተ አይደለም ..... ማነው እንደዚህ ያስተማረህ?

ዳዊት፡- ምንም ንግግር አልፈልግም ቤቴን ልቀቅና ውጣ

ዮሐንስ፡- እንሒድ አባዬ አንተን ትቼ መሒድ አልፈልግም

እመቤት፡- አባቸውንማ አትወስድም

ዮሐንስ፡- በረሃብ ልተገደው ነው እንዴ እኔ እያለሁማ አባቴ በርሃብ አይሞትም

አቶ ጌታቸው፡- ማንም ከዚህ ቤት አይወጣም የምትወጡት እናንተ ናችሁ

ዳዊት፡- የእናቴ ቤት ነው እኔ ደግሞ የእዚህ ቤት ታላቅ የዚህ ቤት ወራሽ ገባህ

አቶ ጌታቸው፡- ለካስ ይቺን ቤት ለመውረስ ነው ይሀን ሁሉ ድራማ

እመቤት፡- የእናቱን ቤትማ የማንም ወፍ ዘራሽ አይወርሰውም

ዮሐንስ፡- እኔ ቤት አልፈልግም አባዬን ይዤው እኖራለው አንተ ግን ከባት አለኝ ብለህ እንዳትፈልገው

አቶ ጌታቸው፡- ቆይ ቆይ ይሒ ቤት የእናትህ ነው ያለህ ማነው በዚህ ቤት ላይ እናትህም አንተም እኔም መወሰን አንችልም መወሰን የሚችለው ዮሐንስ ብቻ ነው

እመቤት፡- ዮሐንስ?

አቶ ጌታቸው፡- አዎ ዮሐንስ! እንደውም ባለውለታችኝ ነው አስከዛሬ በእሱ ቤት ኖረን ኪራይ ባለመክፈላችን .... አዎ ዮሐንስ አባትህ አንተ የ2 ወር ልጅ እያለህ ነው የሞተው ሲሞት ግን ሃብቱን ቤቱን ሁሉ በአደራ መልክ ለአንተ ሰቶኝ ነው የሞተው አንግዲ አሁን ሃያ አመት ሞልቶሃል ውሳኔው የአንተ እንጂ የእኔ አይደለም

ዮሐንስ፡- ይህንን ያደረገ እግዚአብሔር ይመስገን /ዞርዞር እያለ ያያል/ ዛሬ በትንሳኤው ብርቄም የደስታችን ተካፋይ ትሁን ከመጣው ጀምሮ በር በሩን እያየው ነው ምስጢራችንን እንንጋገራለን ብርቄ ..... ብርቄ የለችም እንዴ? አባ ለምድነው የምታለቅሰው ..... ብርቄ ....የለችም እንዴ?

አቶ ጌታቸው፡- የሐንስ ብርቄ ለዚህ ቤት መሰዋዕት ሆናለች ነፍሷን በአብርሃም በይስሃቅ በያቆብ ጎን ያኑራት

ዮሐንስ፡- /ምርር ያለ ለቅሶ ያለቅሳል/ ለምን? ..... ምነው ጌታዬ እመቤቴ ቃላችን እንደዚህ ነበር እንዴ? እናቴ ታዲያ ለምን? እመቤቴ እባክሽ አዘኝላት እሷ ምስኪን ነች ያንቺን ስም እኮ ጠርታ አትጠግብም እናቴ ነፍሷን በአንቺ አድርጊው ፍቅርሽን የማጠግብ ናትና ፍቅርሽን አጥግቢያት ..... ግን እንደት አባ በምን ምክንያት?

አቶ ጌታቸው፡- ምክንያቱን ለእግዚአብሔር ልጄ ..... ግን ለእኔ መድኃኒት ልትገዛ ስትሄድ ነው ጎረምሶች ናቸው አሉ በመንገድ ደሟን ያፈሰሱት

ዮሐንስ፡- /ያለቅሳል/ ተይዘዋል ... እነማን ናቸው?

አቶ ጌታቸው፡- ምን ለእሷ ብቻ ለሶስናም ሞት ተጠያቂ እመቤት ናት

ዮሐንስ፡- ሶስና! /ያለቅሳል/ ለምን? አንቺ ለምን?

እመቤት፡- እኔ አለውቅም

ዮሐንስ፡- የእዚህን ቤት ሰላም አስተሽ የምለቅሽ ይመስልሻል ..... ልቀቂኝ አንተ

አቶ ጌታቸው፡- ዮሐንሴ የኃጢአቶቼው ደም ባአንተ እንዳይተላለፍ የበቀል አምላክ እግዚአብሔር የሰራዋን ይሰጣት

ዮሐንስ፡- አለቃትም አባ አንተን አስነብታ ብርቄንና ሶስናን ገለማ እፋረዳታለው ልቀቀኝ

ሶስና፡- በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ዮሐንስ፡- ሶስና!

አቶ ጌታቸው፡- ሶስናዬ! /ከዛልቶቸው ላይ ተነስተው ይወድቃሉ/

ዮሐንስ፡- እመቤቴ በእውነት አንቺን የያዘ ማዕበል ቢመጣ እንኳን በፍቅርሽ ይቀዝፋል

ሶስና፡- በመጀመሪያ ይቅር በለኝ አባዬ ብትመክረኝ አልመከርኮ ብዬ ንፅህት የሆንችውን ሃይማኖት ክጀ አንተን አሳዝኜ ቅድስት ድንግል ማርያምን ክጀ እንዴት የስቃይ ዘመን ነበር ፅንሱን ለማስወረድ በእመቤት ተመክሬ መድኃኒት ወስደኩኝ በሕይወትና በሞት መካከል ሳለው የእመቤት መልክተኛ ሰው ለእርዳታ ሃኪም ቤት ወሰደኝ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ሴትየዋ አሳከሙኝ ታሪኬንም ስንግራቸው አዘኑ በኋላም መጽሐፍ ቅዱስ አስተማሩኝ አሁን ክርስትያን ሆኛለው እርግጥ ነው አሁን ሱባኤ ስለነበር ቆኖና የለም ለትንሳኤ እናንተን ይቅርታ ጠይቄ ንስሐ እገባለው የእናንተን ሃይማኖት እቀበላለው ይቅር በለኝ አባዬ

ዮሐንስ፡- እመቤቴ ... ፍቅር ነሽ እኮ ለዘላለም ኢየሱስ ሆይ የበረከትህን ፍሬ ዛሬ በቤታችን አፍስስ አንተ ጠፍቅ አባት ሆይ በዚች በዛሬዋ ትንሳኤ የዚህን ቤት ዳግም ትንሳኤ እንዳደረክ በመንግስትህም አስበን

አቶ ጌታቸው፡- ፍቅር የማያልቅብህ አባት ሆይ አሁንስ ትንሽ አድሜ ስጠኝ የልጆቼን ፍሬ የማይበት በትንሽ ነገር አማርሬህ ሞት ተመኝቼ ነበር አሁን ግን ትንሽ አድሜ ስጠኝ

ሶስና፡- እኛ ሁላችን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሶች ነን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ያፈረሰ እርሱ ይፈርሳል ነው የሚለው ቃሉ እግዚአብሔር ልቦናሽን ይመልስ አንተም ወንድም ጋሼ ሚስት ለበሷዘውድ ናት እንጂ አምላክ አይደለችም ሚስትህን አታምልክ አንቺም እንደ እርግብ የዋህ ሆኖ ገብቶ እንደ አባብ መናደፍ የሰው ልጅ ባሕርይ አይደለም የሰይጣን እንጂ

ብርቄ፡- ክርስቶስ ተነስአ እሙታን ..... እንኳን አደረሳችሁ /እጇን ታሽጋ ትገባለች/

አቶ ጌታቸው፡- ብርቄ ልጄ ..... በእውነት የእንቺ አምላክ ድንቅ ነው

ብርቄ፡- ውይ በእኔ ላይ ያለው አላማው ፍቅር ነው አራቤን አዙሮኝ መኪና ውስጥ ገባው ስነታ ሆስፒታል ውስጥ ነኝ ዶክተሮቹን ስጠይቅ ለምን አራስሽን ታጠፊያለሽ ምን አይነት ጭካኔ ነው መርዙ አልሰራ ቢልሽ በመኪና ሲሉኝ ደነገጥኩ መዕናኛችን ከእግዚአብሔር ጠይቄ እንደምንም ወደ ቤቴ ውሰዱኝ ስል ሠባት ቀን ሙሉ ጠያቂ እንዳልመጣ ነገሩን ከዚህ በኋላ ሁለት ቀን ያህል መቆየት እንዳለብኝ ተነገረኝ ከሆስፒታል ስወጣ ጌታዬ ሁሉን ነገር ሠላም እንዲያደርግልኝ ልለመንነው ወደ ቤተ-ክርስትያን ሒድኩ እግዚአብሔር ያከበራቸው ሰዎች ..... በኋላ ወደ ቤታቸው ይዘውኝ ሒዱ ድነምም ሕማምም ስለነበረብኝ እንቅልፍ ይዞኝ ሄደ ስነታ የአባዬ መከራ ፊቴ ላይ ድቅን አለብኝ እያለቀስኩ በፍርሃት መጣው የአባዬን መከራ ላይ በሕይወት የማገኘው አልመሰለኝም ነበር ከውጪ በፍርሃት ..... ስገባ የኔ ጌታ ግን ውስጡን በደስታ መንፈስ ሞልቶት አገኘሁት የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን

ዮሐንስ፡- የቤተሰቤ መበተን የበተሰቤ መከራ ሁሉ የመጣው ባንተ ነው ሞት ይገባሃል ብዬ አልፈርድብህም ነገር ግን አንድ ቅጣት አቀጣሃለው በዘመነህ አባቴን ለመንጠቅ እንዳትሞክር እስከዛሬ በእኔ ቤት ኖረሃል የኪራዩን ዋጋ ዛሬ እንድትከፍለኝ አፈልጋለው ከፍያውም ገንዘብ አይደለም ይሒን የጠንቋይ መንፈስ ይዘህ ከእኛ ..... ቤቴን ለቀህ ውጣልኝ /ዮሐንስ የቤቱን ቁልፍ ከእመቤት ተቀብሎ ለብርቄ ይሰጣታል ዳዊትና እመቤት ቀስ ብለው ሻንጣቸውን ይዘው ይወጣሉ

ዮሐንስ ወደ ብርቄ ተጠግቶ ያቅፋታል ሶስና ለአባቷ ታሰየዋለች አልላቀቅም ሲሉ አቶ ጌታቸው ያስላሉ/

አቶ ጌታቸው፡- እንግዲ የእናትህ ሙት አመት ይከበርና ከዚያ በኋላ ባይሆን አስባለው

ዮሐንስ፡- እመቤቴ ይህን ሁሉ ያረሻሸልኝ እኔ ማንኝ ባክሽ ምልጃሽ አይለየኝ ቤትሽ በመምጣት ይሕን ያህል ደስታ ከተገኘ ለዘላለም በቤትሽ እኖራለው የቅሜርን ማዕበል ባንቺና በልጅሽ በኢየሱስ ክርስቶስ አልፈነዋል

አለፍኩኝ ድንግል ማዕበሉን (ሞገድ ሲመታኝ ማዕበሉ) እየተዘመረ መገራጀው ይዘጋል

የደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ እና ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክርስትያን ሥዓተ-ጥበብ ሰ/ት/ቤት

ድርሰት፡-

ኃይሉ መልከነሙ

ፀሐፍ፡-

ፋሲል ኪዳኔ

(ለመጀመሪያ ጊዜ ሐምሌ **25 2001** ዓ/ም አዳር ተሠራ። በመቀጠልም መጋቢት **21/2002** ዓ/ም በደብሩ ሰ/ት/ቤት አዳራሽ በገንዘብ ታይቷል።**)**

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!

የሕ/ሰ/ቱ/የ/ግቢ ጉባኤ ቪ_ ጥበቦች ክፍል